ናይል

Nile 7th year; publication No.1; November,2020

ናይል 7ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1፣ ህዳር 2013 ዓ.ም

ዶ/ር ኢንጂነር ጌታሁን መኩሪያ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር አውደ ጥናቱን በንግግር ሲከፍቱ

የዘንድሮው የመምህራን ቀን ማጠቃለያ ዝግጅት በባህርዳር ዩኒቨርስቲ ተካሄደ

በሙሉጌታ ዘለቀ

"መምህራን ቀዉስ ለመቀልበስም ሆነ ለመጭው ጊዜ ብሩህነት ግንባር ቀደም ሚና አላቸዉ" በሚል አለም አቀፋዊ መሪ ቃል የተከበረውን የዘንድሮው ዓገር አቀፍ የመምህራን ቀን የማጠቃለያ ዝግጅት ባህርዳር ዩኒቨርስቲ አከናውኗል፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር እና በባህርዳር ዩኒቨርስቲ ትብብር ከጥቅምት 20/2013 እስከ21/2013 በተከናወነው የመምህራን ቀን የማጠለያ ዝግጅት ዶ/ር ኢንጂነር ጌታሁን መኩሪያ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ ርእሰ መሥተዳድር ደረጃ የማኅበራዊ ዘርፍ አስተባባሪና የአማራ ክልል ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ሙሉነሽ አበበ፣ ዶ/ር ዮሐንስ በንቲ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት፣ በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የሰው ሃብትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ሰብሳቢ ወ/ሮ እምየ ቢተውን ጨምሮ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት፣ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች፣ የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ሀላፊዎች፣ እንዲሁም የመምህራን ማህበር ሃላፊዎች ተሳትፈዋል፡፡

በአውደ ጥናቱ በፕሮፌሰር ያለው እንዳወቀ እና በአቶ ደረጀ ታዬ፣ የትምህርት ሙያ በባለሙያውና በማህበረሰቡ ያሉት እይታዎችና የገፅታ ግንባታ አስፈላጊነት፤ በፕሮፌሰር አለማየሁ ቢሻውና በዶ/ር ታደሰ፣ የኢትዮጵያ መምህራን ሙያዊነት፤ በዶ/ር ዳዊት አስራት እና በዶ/ር አንዳርጋቸው፣ የትምህርት ስራ በሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ቀውሶች ወቅት በፕሮፌሰር ረዳ ዳርጌና በዶ/ር አስናቀ ታገለ እንዲሁም በኮቪድ-19 ወረርሽኝ መካከል ሆኖ ማስተማርና የትምህርት ስራን የመምራት ወቅታዊ ጥሪ ትኩረቶች በዶ/ር ይልቃል ከፍአለ የአማራ ትምህርት ቢሮ ሀላፊ ጥናታዊ ወረቀቶች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል::

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንት ዶ/ር ፍሬው ተገኘ ስብሰባውን ሲከፍቱ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አማካሪ ምክር ቤት ስብሰባ ተካሄደ

ገፅ 5

ናይል

በኢንፎርሜሽን እና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት
በውስጥ ግንኙነት እና ኮሚኒኬሽን ክፍል የሚዘጋጅ ወርሀዊ ጋዜጣ

ዋና አዘጋጅ
ትዕግስት መኮንን

ግራፊክስ ዲዛይነር
ትዕግስት መኮንን

ዘጋቢዎች
ሙሉጎጃም አንዱዓለም
ወንዳለ ድረስ
ሙሉጌታ ዘለቀ
ትግስት ዳዊት

ፎቶግራፈሮች
ታምራት አታላይ
በሪሁን ታረቀኝ
ቤተልሄም ወርቅነህ

አምደኞች
ይናገር ተክለስላሴ(ዶ/ር)
ፕ/ር የሺጌታ ገላው
ታምሩ ደለለኝ
ዮሐንስ ዘነበ(ረ/ፕ)
ደስታ ተከስተ
ሂሩት አድማሱ

አርታኢ
አቶ ሀሰን ኡስማን

መልእክተኛ
መልሸው አጥናፉ

ፀሀፊ
መልሰው አደመ
አበባ ካሳው

ሾፌር
ላመስግን ጫኔ

አባይ ማተሚያ ቤት ታተመ
ህዳር 2013 ዓ.ም

Contact us:-
https://www.bdu.edu.et
http://www.twitter.com/bdueduet
https://www.facebook.com/bduethiopia
http://www.linkedin.com/school/bahir-dar-university
+251583209653

ርዕሰ-አንቀጽ

ለተሻለ ነገ የኔ ድርሻ

በታሪክ እንደሚታወቀው ቀደም ባሉት ዘመናት ገናና የነበረችው ሀገራችን ኢትዮጵያ፣ ዛሬ ብዙ የማደግ እድሎች ባሉበት፣ ችግር ፈቺ የተማረ በርካታ የሰው ሃይል በተፈጠረበት፣ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች እዚህም እዚያም በበዙበት በዚህ ዘመን በሰላም እጦት ህዝቡ የሚሰቃይባት ምድር ሆና ማየት እጂግ ልብ ይሰብራል፡፡

"ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ የተሻለ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ በአገራችን መፍጠር ሲገባን እንደሃገር መቀጠል እንኳን አጠራጣሪ የሆነበት ጊዜ ላይ እንዴት ደረስን?" የሚለውን ጥያቄ ጤናማ አእምሮ ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ዛሬ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

መጠኑ ይለያይ እንጂ ፤ አገራችን ዛሬ ላለችበት ተጨባጭ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ፖለቲካዊ ሁኔታ የሁላችንም አስተዋጽኦ እንዳለበት የማይካድ ነው:: በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ! የተወሰኑት ሲሰሩ ሌሎቻችን ቁጭ ብለናል፤ የተወሰኑት ሲያፈርሱ ሌሎች ወይ ዱላ አቀብለናል ወይም እንዳላየ ሆነን አልፈናል፤ የአስተዋጽኦው አይነት እጅግ የበዛ ነው፡፡

ህዝብ በሰላም ወጥቶ በሰላም የሚገባባት፣ ሁሉም ከሚያለያዩት ይልቅ በሚያመሳስሉት ፣ ከሚበታትኑት ይልቅ በሚያስተሳስሩት የጋራ እሴቶቹ ላይ ቆሞ በድህነት ላይ በመረባረብ ለመጭው ትውልድ ብሩህ ተስፋ የሚያስረክብባት ጠንካራ ሀገር እንድትኖር እንዲቻል ዛሬም ነገም ሌሎች ያልሰሩትን ስራ በመቁጠርና በመተቸት ከምናሳልፈው ጊዜ በላይ ዛሬ ላለችበት ተጨባጭ ሁኔታ የራሳችን አስተዋጽኦ ምን እንደነበር ራሳችንን መጠየቅና ለነገም እያንዳንዳችን እንደዜጋ ምን አስተዋጽኦ ማበርከት እንደሚጠበቅብን ማሰብ የሚኖርብን ጊዜ አሁን ነው፡፡

አሁን ላይ አገራችን ያለችበትን ፈታኝ ሁኔታ በመመርመር ሁሉም በቻለው አቅም ወቅቱ የፈጠረውን የቴክኖሎጂ እድል በመጠቀም የመፍትሄ አካል በመሆን ፋንታ በተለይ ከመረጃዎች አሰጣጥ፣ አቀባበልና አጠቃቀም ጋር በተገናኘ የሚታዩ ህጸጾች አብዛኛውን ህዝብ ብዙ ዋጋ እያስከፈሉ መሆኑ ደግሞ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንደሚባለው አይነት ሲሆን ይታያል፡፡

መረጃዎች ከምንም ይምጡ ከማን ምንም ግድ ሳይል እንዳሉ በመውሰድ ስሜት የማራገብ አካሄዶች በህዝብ ዘንድ የእርስ በርስ አለመተማመን የሚፈጥሩና አንዱ ሌላኛውን በጠላትነትና በጥርጣሬ እንዲያይ የሚጋብዙ ሆነዋል፡፡

ማህበራዊ ሚዲያን ስለ መልካምና የሚያቀራርቡን እሴቶቻችን ጠቃሚና አዎንታዊ መረጃዎች መለዋወጫ መድረክ በማድረግ ፋንታ ስለአገር ስለወገን የተሳሳቱ መረጃዎችን ደጋግሞ በመክተብ ዱላ ማቀበያ እያደረጉ አገርን ጭንቅ ውስጥ እያስገቡ ያሉ አካላትን ልብ ብሎ መለየት ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ውስጥ እነዚህን በእሳት ላይ ቤንዚን የሚጨምሩትን አካላት በምንጽፋቸው በጎ ሀሳቦች ወደመስመር ማምጣት ባንችል እንኳን ቢያንስ እኛ ራሳችን እንደግለሰብ በዚህ የስሜት ጎርፍ ገብተን ላለመወሰድ እንጣር፤ መረጃን ስንቀበልም ሆነ ስንሰጥ አልፎም ስንጠቀም በመጠንቀቅ ይሁን!

ምን አይነት ጠጠር የት እጥላለሁ? ለተሻለ ነገስ የኔ ድርሻ ምንድን ነው የሚለውን ጥያቄ መመለስ አገር ለማዳን ዋጋው ከፍ ያለ ነውና!



ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከከተማው ውሃና ፍሳሽ ጥገኝነት ሊያወጣው የሚያስችል ከ127 ሚሊዮን ብር በላይ ወጭ የተደረገበት የውሃ አገልግሎት በዩኒቨርሲቲው የስነ-ምድር ት/ቤት መምህራን ጥናት መሰረት ለውሀ አቅርቦት ዘላቂ መፍትሄ የሚያስገኙትን ሁለት ጉድጓዶች በማስቆፈር ላይ ነው፡፡

የመምህራን ቀን አከባበር... ከገፅ 5 የቀጠለ

የሰውን በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ የትምህርት እና ሥነ-ባህሪ ሳይንስ ኮሌጅ መምህርና ተመራማሪ የሆኑት ዶር አስናቀ ታረቀኝ፡፡
በኛ ሀገር መንግሥት ሃላፊነቱን ወስዶ ሲያከብር የዘንድሮው የመጀመሪያ በመሆኑ በመምህራን ማህበርም ሆነ በውይይቱ ተሳታፊዎች እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሯል፡፡

በመምህራን ማህረበር አዘጋጅነትም ሆነ በመንግሥት ደረጃ ከት/ቤት ጀምሮ እስከ ሀገርአቀፍ ሲከበር ግን መምህራን ትውልድን ለመቅረጽ ያላቸው ጉልህ ሚና ጎልቶ እንዲወጣ ያደርገዋል፡፡

በመምህራ ቀን አከባበር የሚከተሉት ክንውኖች ሊካሄዱ ይችላሉ፡-
- ልዩልዩ የመዝናኖ ፕሮግራሞች ይዘጋጃሉ፤
- በኪነጥበብ ዘርፍ በስፖርት፤ በስዕል፤በስነጽሁፍ፤ውድድሮች ይከናወናሉ፤
- የፓናል ወይይቶች፤ ፎረሞች ኮንፈረንሶችናአውደ
- ጥናቶች መምህራን ራሳቸው በተሳተፉበትሁኔታ ይከናወናሉ፤
- ለመምህራን ልዩ ሰዩ ሥጦታዎች በወላጆች፤ በ ተ ማ ሪ ዎ ች ፤ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ባ ለ ሆ ኑ ድ ር ጂ ቶ ች አ ማ ካ ኝ ነ ት ይሰጣል፤
- ሀገራዊ የሽልማት ሥርዓቶች ተዘርግተው ለምስጉን መምህራን ሽልማትይዘጋጃል፤

በአጠቃላይ መምህራን የሁሉም ሙያዎች ቁልፍስለመሆኑ ይዘከራል፡፡

ለመጭው ጊዜ መልካምነትም ሆነ ብሩህ መሆንም ያለ መምህራን ተሳትፎ ውጤታማ ለመሆን

"On National Teachers' Day, we recognize the countless men and women who dedicate their lives to instilling character, integrity, and knowledge in the hearts and minds of our Nation's students."

_ Trump-president of USA _



የLMS ስልጠና... ከገፅ 5 የቀጠለ

በመጀመርያዉ ዙር 206 መምህራን ስልጠናዉን የወሰዱ ሲሆን ተሳታፊዎችም በሰለጠኑት አግባብ የሚያስተምሯቸውን የትምህርት ግብዓቶች ለተማሪዎቻቸው ሲስተም ላይ ማስቀመጥ ችለዋል፡፡ ይህ በመሆኑም ተማሪዎች ትምህርት ሲጀምሩ የተቀመጠላቸውን የተለያዩ የትምህርት መሳሪያዎች በየትኛዉም ቦታ ሆነዉ ማግኘት እና መጠቀም እንዲችሉ የሚያግዛቸዉ መሆኑ ተገልፆል ፡፡

ዳሬክቶሬት የኮረና ወረርሽ ከተከሰተ በኋላ የሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች መማር ማስተማር ሂደት ሳይቋረጥ በተሳካ ሁኔታ እንዲቀጥል እያደረገ ያለው ጥረት የሚያበረታታ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በተጨማሪም 2 ሚሊየን 150 ሽህ(2,150,000) ብር የሚገመት ዋጋ የሚያወጣ የትምህርት ማስተዳደሪያ ስርዓት ስርዓት/Learning Management System/ ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ማስረከቡ

የዩኒቨርሲቲያውአይ.ሲ.ቲ ይታወሳል፡፡

ከዝግጅት ክፍሉ፡-

ጋዜጣችንን ከአዘጋጆችዋ ዓይነተኛ ፋላጎት እና የሙከራ መድረክነት አላቆ ስብጥሩ ለበዛው ታዳሚ ተደራሽ፣ ትክክለኛ የመረጃ እና የእውቀት ምንጭ ለማድረግ የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራሮች እና የዝግጅት ክፍሉ ባልደረቦች ከመቸውም ጊዜ በተሻለ ቁርጠኞች ሆነዋል፡፡

የቀደመውን የአሰራር ሂደት በባለሙያዎች፤ ድክመት እና ጥንካሬውን ለመለየት ተሞክሯል በዚህ መነሻነትም በጋዜጣዋ ይዘትና አቀራረብ ላይ መጠነኛ ለውጦች ተደርጓል፡፡
ለውጡም በታላሚ ተደራሾች ያልተቋረጠ ተሳትፎ ወደ ሚፈለገው ደረጃ ይደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡

መልካም ንባብ!!

ይህ አምድ ከዜናዎች በተጨማሪ ወቅታዊ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ሀተታዊ ፅሁፎች ይቀርብበታል

ሠሞነኛ

ለመምህራን የመጀመርያ ዙር የLMS ስልጠና ተሰጠ

በሙሉጎጃም አንዱwአለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስልጠና ዳይሬክቶሬት ከዩኒቨርሲቲዉ የአይ.ሲ.ቲ. ዳይሬክቶሬት እና ከአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ተመራቂ ተማሪዎችን ለሚያስተምሩ ቅድሚያ በመስጠት ከጥቅምት11-24/2013 ዓ/ም በሁሉም ግቢ ለሚገኙ መምህራን የLearning Management System (LMS) ስልጠና ሰጥቷል ፡፡

ወደ ገፅ 4 ዞሯል

"የኢትዮጵያ የሳይንስ ሳምንት"

በተባበሩት መንግስታት የትምህርት ሳይንስ እና ባህል ድርጅት ኖቬምበር 10 በአለም አቀፍ ደረጃ የዓለም ሳይንስ ቀን ተብሎ በተለያዩ ተግባራት ይከበራል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስተር "የዓለም የሳይንስ ቀን" መሰረታዊ እሳቤዎችን ከሀገራዊ የሳይንስ ባህል ግንባታ ስራዎች ጋር በማስተባበር በሀገር አቀፍ ደረጃ "የኢትዮጵያ የሳይንስ ሳምንት" በሚል ስያሜ ከጥቅምት 27/2013 እስከ ህዳር 4/2013 በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች እንዲከበር በሰጠው አቅጣጫ መሰረት ዩኒቨርሲቲዎች ሳምንቱን በተለያዩ ክንዎኖች በማክበር ላይ ይገኛል፡፡

ከሳይንስ ሳምንት ቀናት መካከል ህዳር 2/2013 "የሴት ሙህራን ቀን" ተብሎ በምርምርና ማ/ሰብ ዳይሬክተር ዶ/ር ነፃነት ባይሮ አስተባባሪነት በተለያዩ ዝግጅት ተከብሯል፡፡

የሴቶች ምሁራን ቀን በአገራችን ለሁለተኛ ጊዜ በዩንቨርስቲዎችን ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የሴት ምሁራን በዩንቨርስቲው እና በማህበረሰቡ የሚያደርጉትን አስተዋጾ ከፍ ለማድረግ እና በጥናት እና ምርመር ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ ሴት ምሁራን ውይይት አድርገዋል፡፡

የሴት ምሁራን ቀንን በማስመልከት እና ከሌሎች ዓመታት በተለየ በ2012 ዓ.ም በርከት ያሉ ሴት የዩኒቨርሲቲዎችን መምህራን በሶስተኛ ዲግሪ መመረቃቸውን ምክንያት በማድረግ ናይል ጋዜጣ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት ወስኗል፡፡

ገፅ 16ን ይመልከቱ

የመምህራን ቀን አከባበር ፋይዳ እና ታሪካዊ ዳራ

በሙሉጌታ ዘለቀ

ስለ መምህራን ቀን ሲወሳ ከቀኑ በስተጀርባ ያለውን ባለታሪክ ህንዳዊ ዶ/ር Sarvepalli Radhakrishnan ግድ ይላል ፡፡

እ.ኤ.አ በ 1888 ህንድ ውስጥ ቲሩታኒ በምትባል ቦታ ከመካከለኛ ቤተሰብ የተወለዱት እኒህ ሰው ለበርካታ አመታት በመምህርነት ያገለገሉ ሲሆን እ.ኤ.አ በ 1947 ህንድ ነፃነቷን ስታገኝ ህንድን በዩኔስኮ ወክለው (1946 - 52) አገልግለዋል፡፡ እ.ኤ.አ በ1952 ዶ/ የህንድ የመጀመሪያ ምክትል ፕሬዝዳንት ሆነው ተሹመዋል ፡፡

በ20ኛው ክፍለዘመን የንዕዕር ሃይማኖት እና ፍልስፍና በጣም ከታወቁ ምሁራን አንዱ ነበሩ፡፡ በስነጽሑፍ ለኖቤል ሽልማት 16 ጊዜ ፣ ለኖቤል የሰላም ሽልማት 11 ጊዜ ተመርጠዋል፡፡

የስራ ባልደረባው ለህንድ ላደረገው ያልተገደበ አስተዋፅዖ የልደት ቀኑ እንዲይከበርለት ቢጠይቁትም "ልደቴን ከማክበር ይልቅ መስከረም 5 የመምህራን ቀን ሆኖ ቢከብር የእኔ ኩራትና መታደል ነው " ብለዋል፡፡

ለዶ/ር ሳርቬፓሊ ራዳክሪሽናን እና ለመላው መምህራን ክብር እና መታሰቢያነት ሲባል የመምህራን ቀን የማክበር ባህል እ.ኤ.አ ከ 1962 ጀምሮ በህንድ ተጀመረ ፡፡

የመምህራን ቀን 1966 ILO (international labour organization) ምክረ ሃሳብና UNESCO, 1966 ካጸደቀው ውሳኔ በመነሳት የመምህርነት ሙያ በማህበረሰቡ ተገቢ ሥፍራ እንዲያገኝ ከመሻት የመነጨ ነበር፡፡
በጊዜው ለመያው የሚያስፈልጉ መሰረታዊ እሳቤዎች ከማስቀመጥ አልፎ ከመምህራን ስለሚጠበቁ ሃላፊነቶችና ግ ዴ ታ ዎ ች ን አ መ ላ ክ ተ ዋ ል ፡ ፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በመምህራን ም ል መ ላ ና ሥ ል ጠ ና ፤ አ መ ላ ካ ች ነጥቦችን በመሰንዘር፣ የተጀመሩትን በማድነቅ የጎደሉትን ደግሞ በማሳሰብ በየዓመቱ በሚደረግ አከባበር ለማስተካከል ሀገራትና መንግሥታት እንዲተጉ በማድረግ ረገድ አከባበሩ አስተወጽኦ ነበረው፡፡

ዓለማቀፋዊው የመምህራን ቀን በፓሪስ ጥቅምት 5 ቀን የሚከበር ሲሆን፤ በሌሎች የዓለም ሀገራት ግን በመምህራን ሳምንት ወይም ዕለት አመች ጊዜ ወስነው የማክበር ልማድ አለ፡፡
የአንድ ሙያ ባለቤቶችን በተደራጅና በታቀደ ሁኔታ ማክበርበርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

የመምህራን ቀን ማክበርም የመምህርነት ሙያን ማህበረሰቡ እንዲያከብረው ብቻ ሳይሆን ተተኪው ትውልድም መምህርነትን የመጀመሪያ ምርጫው አድረጎ እንዲወስድ ያነቃቃል ተብሎ ይታመናል፡፡

መምህራን የተቀደሰ ሙያቸውን በ ሚ ያ ከ ና ው ኑ በ ት ጊ ዜ የሚያጋጥሟቸውን ሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሮአዊ ተግዳሮቶች በማሰስ የሚፈቱበትን መንገድ ቢጋራ ይመክሩበታል፡፡

ሴቶችን፤ እና አካል ጉዳተኞችን በ ት ም ህ ር ት ተ ደ ራ ሽ ሲ ያ ደ ር ጉ በሚችሉ ጉዳዩች ዙሪያ ይወያየበታል፤ በመንግሥትና በሁሉም ማህበረሰብ በኩል ለመምህርነት ሙያ ተገቢው ክብርና ዝና ተጥሶ ቢገኝእንዴትካክል ጥሪዎች ይስተጋቡበታል፡፡

የሙያው ባለቤት የሆኑት መምህራን በተገቢው ዕውቀት፤ ክህሎትና አመለካከት የበለጠ በማብቃት ሰጥራት እንዲሰሩ እገዛ የሚደረግባቸውን ሥልቶች ቢጋራ ይቀይሰበታል::

ለዘላቂ ልማት መምህራን የሚጠበቅባቸውን ተልዕኮዎች፤ ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ይመጥን ዘንድ የአጋር አካላት ድጋፍ እና ሚና ዙሪያ ሀሳብ ያንጸባርቅበታል፡፡

ባሳለፍነው ሳምንት የተከበረው የመምህራን ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረገውን ዙር ለማወቅ ከ1966 ጀምሮ መቁጠር ይጠይቃል::

በኢትዮጵያ ግን አልፎ አልፎ የሚቋረጥበት ሁኔታ ቢኖርም ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ እየተከበረ ይገኛል ይላሉ ለዚህ ዕሁፍ መረጃ

ወደ ገፅ 4 ዞሯል

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አማካሪ ምክር ቤት ስብሰባ ተካሄደ

በትዕግስት ዳዊት

የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ወደ ተቋሙ በሚመለሱበት ወቅት የሚኖረውን የአቀባበል ሁኔታ ለመወሰንና አቅጣጫ ለማስቀመጥ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የመክረው የባህርዳር ዩኒቨርስቲ አማካሪ ምክር ቤት ጉባኤ ሰሞኑን ተካሂዷል፡፡

የባሕር ዳር ከተማ ከንቲባ ዶ/ር ድረስ ሳህሉ በመሩት በዚህ ጉባኤ ሁሉም የከተማው አስተዳደርመምሪያዎች የድርሻዎችን እንዲወጡ ተጠይቋል፡

የሃይማኖት ተቋማት፣ የሃገር ሽማግሌዎች የንግዱ ማኅበረሰብ የከተማውንወጣትናየሚመለከታቸውን ሁሉ አስተባብረው እንዲሰሩ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

የኢፌዲሪ ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ዩኒቨርሲቲዎች የአማካሪ ምክር ቤት እንዲያቋቁሙ በሠጠው አቅጣጫና በተላከው የአሠራር ማዕቀፍ መሠረት በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ 33 አባላትን ያቀፈ አማካሪ ምክር ቤት ማቋቋሙ ይታወሳል፡፡

ትርጉምን ፍለጋ... ከገፅ 7 የቀጠለ

ደረጃ3.Depersonalization (ስብዕና-ነጠቃ)

እዚህ ደረጃ ላይ አስረኞች ሁሉም ነገር ህልም ውስጥ ሆኖ እንደሚታይ ሊሆን የማይቻል እውነታ ውስጥ የገቡ ያህል እንደተሰማቸው ተርጓሚው ይገልጹልናል፡፡በመጀመሪያው ቀን በተባበሩት ሀይሎች (Allied Forces) ነፃ ወጥተው መስኩንም ሀገሩንም ቢያዩትም የጠበቁትን ደስታ አላገኙትም፡፡

ይህም የሆነው ለረጅም ጊዜያት በከፍተኛ ጫና ዉስጥ የነበረ ሰው ጫናው በድንገት ሲቋረጥበት በሞራልና መንፈሳዊ ጤናው ላይ ጉዳት ሊደርስበትና ሊሰቃይ ስለሚችል ነው:: በዚህም ምክንያት ብዙም ያልዳበረ ተፈጥሮ የነበራቸው ሰዎች በክምፕ ህይወታቸው ከቧቸው የነበረውን አረመኔያዊ ተዕእኖ በቀላሉ ሊላቀቁት እንዳልቻሉ ተስተውሏል፡፡

አሁን ነፃ ስለሆኑ ይህን ነፃነታቸውን ያለገደብ ያለማመንታት ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ አስበው ከተጨቋኝንነት ወደ ጨቋኝነት መሸጋገሪያ ስሜት ላይ ነበሩ:: በተጨማሪም ከፍተኛ ምሬትና ግራመጋባት ስሜት ውሰጥም ገብተው ነበር፡፡

ወደ መደበኛ ህይወት ሲመለሱ የደረሰባቸውን መከራ የሚረዳላቸውና የሚያምናቸው አለመኖሩ ብሎም ከአንግዲህ ወዲያ የህይወት መከራ አብቅቷል ብለው ሲጠብቁ ህይወት እንደገና ከእነሱ ስትጠብቅ፣ ወላጅ፣ ዘመድ፣ ጓደኛን እናገኛለን ብለው አስበው ያልጠበቁት ሲከሰት፣ ስቃዩን ለመቋቋም ሲቸገሩ ታይቶ እንደነበር ተርጓሚው ይገልጻሉ፡፡

የመጽሐፉ ሁለተኛ ክፍል

የመጽሐፉ 2ኛ ክፍል ግለ-ታሪኩን ያነበቡ ሰዎች የህክምና ፍልስፍናውን ቀጥተኛና ሰፋ ያለ ማብራሪያ ስለፈለጉ
ከሞት ካምፕ ወደ ህልውናዊነት (From Death Camp to Existentialism) ከሚለው መፅሀፉ ላይ ስለ ሎጎ-ቴራፒ ጨምሮበት ትርጉምን ፍለጋ በሚለው መፅሀፍ ውስጥ ያካተተውን የሚዳስስ ነው፡፡

ሎጎ-ቴራፒ በሚለው ስያሜ ውስጥ ሎጎ የሚለው ቃል የተወሰደው ከግሪክ ሲሆን ፍቺው ‹‹ቃል፣ትርጉም፣ ስራ፣ድርጊት ወዘተ›› የሚወክል ሲሆን ፍራክል ትርጉም የሚለውን መርጧል፡፡
በመግቢያው እንደተጠቀሰው ሎጎ-ቴራፒ 3ኛው የቪየና ሳይኮ-ቴራፒ አስተምሮር ሲሆን በሰዎች ውስጥ ከሚገኙት የተነሳሶት ሀይሎች ውስጥ ቀዳሚው ሀይል ትርጉምን የመሻት(Will to meaning) መሆኑን የሚያስረዳ አስተምሮር ነው፡፡ ሰብዙ ሰዎች ሎጎ-ቴራፒ መባሉ ግራ መጋባትን ፈጥሯል፡ ህመምን ማዳን ብቻ ተደርጎ በመታየቱ፡ሎጎ-ቴራፒ የህልውና ትንተና ነው፡፡

ሰው መሆንንና የሰውን አቅም ማዳበር ላይ የሚያተኩር አስተምሮር ነው፡፡

በዚህም ሰው ስራሱ ብቻ ልዩ የሆነ ትርጉም ለሚሰጡት አላማዎችና እሴቶች የሚኖር ፍጡር ነው ብሎ የሚያስብ ነው፡፡ ሰው ቢያንስ ከ3 ምንጮች ትርጉምን ያገኛል ይላል፡፡

ከስራ፡ ከፍቅር (ተፈጥሮን ውበትና ጥበብን ማጣጣምን ጨምሮ) እና ከስቃይ ራስን ለአንድ አላማ /ተልዕኮ/ በመስጠት በሚደረግ ስራ ወይም ጥረት ውስጥ ትርጉም ይገኛል፡፡

ለምሳሌ እንደ ፍራንክል የአእምሮ መቃወስ ያለባቸውን በሽተኞች በመርዳት፣ ሁለተኛው ከግል ፍላጎት በመሻገርና ለሌሎች በመኖር ልክ ፍራንክል ለአባቱ ሲል ቪዛውን እንዳቃጠለው፣በመጨረሻም ከስቃይ ይገኛል ልክ ፍራንክል በማጎሪያ ካምፕ አስቃቂ ህይወት ውስጥ ማለፉ የሰውን ዝቅታና ከፍታን ለማየትና የምንወያይበተን መጽሐፍ ለመፃፍ እንዳበቃው፡፡
የሎጎ-ቴራፒ ንድፍና ሀሳብ መሰረታዊ አሳቤዎች፡-

1. ህይወት በማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔታም ቢሆን ትርጉም አላት፡፡
2. ህይወት ሁሌ ጥያቄ ሳይሆን ምላሽ ትጠብቃለች፡፡ ስለዚህ ከህይወት ምን ሰጠኝ ሳይሆን ምን አደረኩላት የሚለው ጥያቄ ትክክለኛው ነው፡፡
3. ሰዎች ትርጉምን የመሻት ፍላጎት አላቸው፡፡
ይህም ፍላጎት ለመኖርም፣ ለመስራትም ዋና አንቀሳቃሽ ሀይል ነው፡፡
4. ሰዎች በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ትርጉም ለመፈለግ ነፃነት አላቸው:: ነባራዊ ሁኔታን እንኳን መቀየር ባይችሉ አመለካከታቸውን መቀየር ይችላሉ፡፡

5. ሰዎች ውሳኔያቸውን ትርጉም ያለው እንዲሆን ከፈለጉ የህይወትን ጥያቄ መመለስ አለባቸው፡፡ በህይወት ውስጥ ስንንዝዝ አያንዳንዱ ገጠመኝ ትርጉም ልናገኝበት የምንችለውን ዕድል ይሰጣል፡፡ (Meaning Potential)

የመጨረሻውን ግብ ልክ እንደ አድማስ ልንጠጋው እንጂ ልንነካው ባንችልም የወቅቱን ትርጉም (The meaning of the moment) ልናገኝና ልናሳካ እችላለን፡፡

6. እያንዳንዱ ሰው የማይተካ ልዩ አስፈላጊነት አለው፡፡

ሰው ትርጉም የሚያጣበት ሁኔታ ነፃነት ካጣ፣ ትርጉምን መፈለግ ከከበደው፣ ከተወውና ለመርሳት ከሞከረ ህልውናዊ ወናነት (Existential vacuum) ውስጥ ይገባል፡፡

> **“He who has a why to live for can bear almost any how”**
>
> **_ Nietzsche**

ሀኪም ከተገኘ... ከገፅ 8 የቀጠለ

ሀገርም እንደዚሁ ናት መልካም ያልሆኑ ዜጎች በበዙ ቁጥር ተግዳሮቶቹም ያንኑ ያህል ዘርፈ ብዙ ናቸው፡፡

ዘረኝነትና ሙሰኞች የበዙባት ሀገር ሁል ጊዜ ለህመም ትዳረጋለች፡፡
ችግሩ ከከፋም እንደ ሀገር የመቀጠል ህልውናዊ ሊያክትም ይችላል፡፡

አሁን ላይ በሀገራችን የምናስተውለው ጉዳይ መለያየትን አላማ አድርገው ጠዋት ማታ በየማህበራዊ ሚድያዎች ላይ እንደ ቁራ የሚጮሁ አንዳንድ አክቲቪስት ተብዬዎች፣ በተለያየ ጊዜ የሀገሪቱን አንጡረ ሀብት የዘረፉ ናቸው በተለያየ ወንጀል ያደፉ ጉዳቸው እንዳይጋለጥ በአንድም በሌላ መንገድ ሀገርን እንዳትረጋጋ በድብቅ የሚያሴሩ ጥቅመኛ ሹመኞች በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሀሰት ትርክት የሚደስኩሩ አንዳንድ ምሁራን ተብዬዎች የዘመናችን የትውልዱ አራሙቻዎች ይመስሉኛል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ሀገራችን ኢትዮጵያ በየትኛው ዘመን ቢሆን አይነቱና መጠኑ ይለያይ እንጅ ከችግሮች ፈተና ፀድታ አታውቅም፡፡

የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ ፈተናዎች ሲያጋጥሟት ኖራለች፡፡ እያጋጠሟትም ነው፡፡
ይሁንና አንድም ጊዜ በችግሮች ሳቢያ ወድቃም ፈርሳም አታውቅም:: ልትፈርስም አትችልም፡፡

ጥቂቶች ከግል የስልጣን ጥመኝነትና ሀብት ለማጋበስ ከመቋመጥ የተነሳ “እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል” ከሚል እንሰሳዊ አሳቤ ሀገርን አደጋ ላይ ጥለዋል፡፡ ቢሆንም ኢትዮጵያን የሚጠብቃት ፈጣሪ ለዕኩይ አላማቸው አሳልፎ አልሰጣትም፡፡

በአሁኑ ወቅትም ቢሆን እንደ ሀገር ለገጠመን ችግሮች መፍትሄ አምጭ ትተ ዜጎች ስላሉን ተስፋችን የላቀ ነው፡፡ የታመመ ሁሉ አይሞትም አንድም በዘመናዊ ህክምና አልያም በባህላዊ መንገድ መድሀኒት አግኝቶ ይፈወሳል፡፡

ሀኪም ከተገኘ በሽተኛ ይድናል ብለን እናምናለን፡፡ ኢትዮጵያን አስተሳሰብ የበኩላችን አስተዋጽኦ ካበረከትን ሀገር ከህመሟ መፈወሷ አይቀሬ ነው እናንተ ዛሬ ሀገሬ ያጋጠማትን ፈተና አልፎ እንድትቀጥል ሌትና ቀን የበኩላችሁን ድርሻ እየተወጣችሁ ያላችሁ ሁሉም ሁሉን፣የሀገር ሽማግሌዎች፣የሀይማኖት አባቶችና ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የዚህ ጽሑፍ ባለቤት ለእናንተ ትተ የሀገር ሀኪሞች ያለኝን ክብርና አድናቆት ከልብ ልገልጽ እወዳለሁ፡

በዚህ ዘመን የሀገራችን ዋልታና ማገር ናችሁና ፈጣሪ ፀጋውን ያብዛላችሁ እናንተ እስካላችሁ ድረስ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ቅርብ እንደሆነ ይታየኛል፡፡

እጅ ከምን

በዚህ አምድ የዩኒቨርሲቲው ባልደረቦች እጅ ከምን ስንል አለን የምትሉት ለአንባቢ የሚበቃ ዕሁፍ ይስተናገድበታል

ትርጉምን ፍለጋ ዳሰሳ

በታምሩ ደሰለኝ
ሳይኮሎጅ ት/ት ክፍል ባ/ዳር ዩኒቨርስቲ

‘Man’s Search for Meaning’ በሚል ርዕስ በፕ/ር ቪክቶር ፍራንክል የተደረሰውና “ትርጉምን ፍለጋ” በሚል በዶ/ር ፀሀይ ጀምበሩ የተተረጎመው የ 122 ገፅ መፅሀፍ በታምሩ ደሰለኝ እንደሚከተለው ተዳሷል፡-

In the beginning was logos, in the year 2000 is logo therapy. ቪክቶር ፍራንክል (1905 — 1997) የቬና ሳይካትሪስትና ኒውሮሎጂስት ሲሆን በስፋት ሎጎ ቴራፒ ተብሎ የሚታወቀውን የህልውናዊነት አስተምሮር (Existential School of Thought) መስራት ነው፡፡

የመጀመሪያው የቬና ሳይኮቴራፒ አስተምሮር ሰው የሚንቀሳቀሰው ፍስሃን /ኦርካታን/ በመሻትና ስቃይን ለመራቅ ነው (will to pleasure) የሚለው የሲግመንድ ፍሮይድ ሳይኮ አናሊሲስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የፍራንክል መምህር የሆነው አድለር ኢንዲቪጅዋል ሳይኮሎጂ (ግለሰባዊ ሰነ-ልቦና) የሰው መሰረታዊ ተነሳሶት ከሀይል ፍላጎት (will to power) የሚመነጭ ነው የሚለው ነው፡፡

በዚህ ምክንያት መጨረሻ የመጣው የፍራንክል እሳቤ ሶስተኛው የቬና ሳይኮ-ቴራፒ አስተምሮር ተደርጎ ይታያል:: የፍራንክል አስተምሮር የሰው መሰረታዊ ተነሳሶት (motivation) የሚመነጨው ትርጉምን ከመሻት (will to meaning) ነው የሚል ነው፡፡ በእሱ እይታ ሰው ብቸኛው ትርጉምን የሚሻ እንስሳ ነው፡፡

የትርጉምን መፈለግ መሰረታዊነት ለማሳየት በቀላሉ ሁለት ጥናቶችን ይጠቅሳል፡፡የመጀመሪያውየጆን ሆፕኪንስ ዩኒቨርሲቲ በ 48 ኮሌጆች በሚገኙ 7948 ተማሪዎች ላይ ባደረገው ጥናት ‹‹በጣም አስፈላጊያቸው ነገር›› ምን እንደሆነ ሲጠየቁ 78% የሚሆኑት ተማሪዎች ምላሻቸው ‹‹ለህይወት ግብና ትርጉም ማምጣት ነው›› ሲሉ 16% የሚሆኑት ግን ‹‹በርካታ ገንዘብ ሰርቶ ማግኘት›› እንድሆነ ገልጸዋል፡፡

ፈረንሳይ በተካሄደ ሌላ ጥናት ደግሞ 89% የሚሆኑት መላሾች ሰው ለመኖር የሚያገለግለው ‹‹የሆነ ነገር›› ሊኖረው እንደሚገባ መልስ ሰጥተዋል፡፡61% የሚሆኑት መላሾች በህይወታቸው ውስጥ ሊኖሩለት የሚሹት አንድ የሆነ ነገር ወይም አንድ ሌላ ሰው እንደሚገኝ እና እንዳውም ሊሞቱለትም ወደ ኋላ እንደማይሉ ገልፀዋል፡፡

በርግጥ ፍራንክልም መጀመሪያ ወደ አሽዊትዝ ሞት ካምፕ በመቀጠል ወደ ዳካው እንዲጓዝ ያደረገው የሚኖርለት ሰው ስለነበር ነው፡፡ ምንም እንኳን የአሜሪካን ቪዛውን ተጠቅሞ ከሰቆቃው መትረፍ የሚችልበት እድል ቢኖርም ቤት ውስጥ ያገኘው የአስርቱ ትዕዛዛት ስባሪ ፊደል (ከቬና ቤተ-መክራብ ዘረፋ የተገኘው) በአባቱ ‹‹አባትህን አክብር እናትህንም አክብር በምድሪቱም ዘመንህ ረዥም ሊሆን ይችላልና›› የሚለው እንደሆነ ሲነግረው እድሜውን የሰዋለትን ሎጎ-ቴራፒ ንድፍ ሀሳቡን አሜሪካ ተገዞ ታዋቂ በማድረግ ፋንታ ለወላጆቹ ታማኝ ልጅ በመሆኑ አብሯቸው በናዚዎች ታፈሰ ሚስቱን፣ እናቱን፣ አባቱንና ወንድሙን ከአሽዊትዝ ሞት ባይታደጋቸውም ከጥናቶች ሪፖርትና ከሞት ካምፕ ምክኒያቶች በተጨማሪ ስለ መጽሐፉ ሽያጭ ስኬት በሚጠየቅበት ወቅት የሚሰጠው ምላሽ ትርጉምን መፈለግ ተነሳሶት መሰረታዊ ግሬት መሆኑን ማረጋገጫ እንደሆነ ይገልጻል፡፡

እንደ ፍራንክል ከሆነ በእንግሊዝኛ ብቻ ከ10 ሚሊዮን ቅጂ በላይ ብሎም በ 26 ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎሙ እንዲሁም በላይበራሪ ኦፍ ኮንግረስ በ1991 በአሜሪካውያን ህይወት ላይ ከፍተኛ ተዕእኖ ካሏቸው እንደ መጸሐፍ ቅዱስ ካሉት መፅሀፍት ጋር ተወዳደሮ 8ኛ መሆኑ የመፅሀፉን ይዘት ምን ያህል ከዘመኑ ህብረተሰብ አእምሮ ቀውስ (Neurosis of the mass or psychopathology of the normalcy) ወይም ከተዘነጋው ትርጉምን የመፈለግ ስቃይ ጋር (The unheard cry for which humans must learn to listen) እንደሚገናኘ ያሳያል፡፡

በእርግጥ ፍራንክል መጀመሪያ ስሙን እንኳን ሳያትምበት በ9 ቀን ፅፎ በ1945 ለህትመት ያበቃው መጽሐፍ ትኩርት ያላገኙ ተራ እስረኞችን የዕለት ተዕለት የማጎሪያ ካምፕ የስቃይ ህይወት ብቻ ለማሳየት አልሞ የጻፈው ነበር፡፡

የመጽሐፉ የመጀመሪያ ክፍል

ተርጓሚውበዚህ ክፍል ፍራንክል የራሱን እና ተራ እስረኞችን የዕለት ተዕለት ሰቆቃዊ ህይወት የሚዳስስበትን ሁኔታ ያሳየናል:: እግረ መንገዳቸውን ተስፋን ያልሰነቁ እስረኞች ዕጣ ፈንታ ትርጉምን ከሚፈልጉት አንጻር እንዴት ወደ ታችኛው የእንስሳነት ደረጃ (Primitive Level) እንደሚወርድም ያሳየናል፡፡
በጥቅሉ የሚያልፉበትን 3 የስነ-ልቦና (ሳይክ) ምላሽ ደረጃ ያስረዳል፡-

ደረጃ1. ድንጋጤ-ንዝረት (Shock)

በዚህ ደረጃ በአውሮፓ ያሉ አይሁዳዊያን ከመታፈስ ጀምሮ በባቡር ታጭቀው ለብዙ ሌሊትና ማዕልት ተጉዘው አሽዊትዝ ሞት ካምፕ እስኪደርሱ ድረስ የነበረባቸው ጭንቀት፡ ፍርሃት እና ድንጋጤ ይታያል፡፡

በተጨማሪም በደረሱ ማግስት 90% የሚሆኑት ዛይክሎን ቢ በተባላ ፀረ-አረም ገላቸውን እንዲታጠቡ ተደርጎ ማቃጠያ ክፍል (Crematoria) ሲወረውሩ ሽታው የሚፈጠረውን ድንጋጤ ያትታል፡፡

የተረፉት 10% ቁራጭ ዳቦና ውሃ የሆነ ሾርባ ተሰጧቸው በበረዷማው አየር ውስጥ ለብዙ ሰዓታት መስራት፣ በትንሽ ክፍል ውስጥ ለብዙ ተደራርቦ መተኛት፣ በረባ ባልረባው መደብደብ፣ መሰደብና መዋረድ ብሎም ንብረትን በሙሉ የራስን ፀጉር ሳይቀር ማስረከብ በሚካሄድ ጊዜ ያለውን ስሜት ያጋራል፡፡

በፍራንክል የካምፕ ህይወት ይህ የሳይክ ምላሽ ደረጃ የሚያበቃው ለብዙ አመታት የደከመበትን የሎጎ-ቴራፒ ጥናት ሲያስረክብና በስመ ሳይሆን ለሚቀጥሉት 3 የአስር ዓመታት ቆዳውና ልብሱ ላይ በታተመው ቁጥር (119104) መጠራት ሲጀምር ነው፡፡

ደረጃ2. ምንገዴነት (Apathy)

እዚህ የስነ-ልቦና ምላሽ ደረጃ ላይ ሲገቡ ስሜቶቻቸውበሙሉ ሞተዋል:: ራሳቸውን በየቀኑ ከሚያዩት ድብደባ፣ ጭፍጨፋ፣ የቤተሰብ ናፍቆት ወዘተ ከሚያደርስው ጭንቀትለመጠበቅ ሲባል ማዘን ቀርቷል፡፡

አብዛኛው እስረኛ ወደ ዝቅተኛው የእንስሳነት ደረጃ ወርዷል:: የሚያስበው የሚያልመው ሀሜትን እንኳን የሚያደርገው ስለ ምግብ ብቻ ነው፡ ሕይወቱን ስለሚታደግለት፡፡

በዚህ ረገድ ከመካከላቸው አንዱ እስረኛ በተቅማጥ በሽታ ከሞተ በኋላ ፍራንክል ስለራሱ የሚከተለውን ያስታውሳል፡-አንደኛውእስረኛ የሚቸን ትርፍራፊ ድንች ጨምድዶ ያዛው፡፡

ሁለተኛው የዕንጨት ጫማዎቹን ከእርሱ እንደሚሻሉ አስቦ ቀየራቸው፡፡ ሶስተኛው ኮቱን ገፎ ለብሶ የራሱን ለራሳው አለበሰው፡፡ ሌላው ደግሞ ደህነኛ የጫማማሰሪያዎችን በማግኘቱ ፈነደቀ፡፡ ምንገዴነት (Apathy) ስሜቶችን አፍኖ ስለሚይዛቸው ከእንስሳዊ ፍላጎት ውጪ አስረኛው ለምንም ነገር መጨነቅ እንዲያቆም

ወደ ገፅ 6 ዞሯል

ባህረ_ሃሳብ

ይህ አምድ የተለያዩ የሀሳብ ልዩነቶችን የሚያንፀባርቁ ዕሁፎች፣ ትዝብቶች እና ክርክሮች ይቀርብበታል

Staff Reticent about Providing Information

By Yinager Teklesellassie(PhD)
Humanities Faculty

One of the challenges I faced when I was coordinator of quality assurance in my faculty and now as director of publication and documentation in the office of the RCSVP is the unwillingness of my colleagues to provide information when requested.

I think this is a general tendency of the academic staff of the university. I am also guilty of not providing the information I was asked for many times in the past.

This reticence to give information on the part of the staff is observed in many situations. For instance, it could be when the staff is required to comment on a new draft guideline or by-law which can affect the promotion or the working condition of the staff.

I usually ask the staff for information through email and the response of most of the staff is outright silence. I think we have to know the causes of this reticence to share or provide information and find ways which can facilitate the efficient flow of information in very academic unit or at university level.

I think one of the causes of the problem, I am sorry to say this, is lack of accountability on the part of the staff. We know that we will not pay any price for not providing information however useful the information requested is.

I don't remember an occasion when a staff member was penalized or reprimanded for not providing the information or document that was requested.

I think the other cause of reticence about providing information or submitting documents is lack of trust in the system.

Some teachers may think that the information they provide may not be taken seriously or may be misused, or they may think that they will not be given credit for the information or document they have offered.

The other worrying cause of unwillingness to provide information could be teachers' apathy in the whole educational process.

Teachers may think that the quality of education has reached such a low point that whatever they do will not bring about any change, so they may think that providing the information that is requested by the university administration is just a waste of time.

Even if teachers may think that the information or document they are requested to provide will not solve anyproblem,

> **"I urge all the academic staff to stop being apathetic and distrustful when it comes to providing information to colleagues or to people in the administration and respond to requests for information readily"**

I think they have to respond to the request stating their decision and explaining their reasons.

We even have a moral obligation to give information such as in the case of completing a questionnaire for a study. Not providing information by completing a questionnaire could be very unethical, particularly when completing the questionnaire does not take more than fifteen or twenty minutes.

Sometimes the information we have to provide can be necessary to make a decision by the university administration which can affect our future or career. Or the information we withhold or the document we are not willing to share can stall the work of others.

Thus, we have to make every effort to respond to requests for providing information or sharing documents.

Frequently, what is requested, for example in the case of giving comments on a draft guideline or by-law, may demand a lot of time and energy. In that case what we can do is to focus on a specific article or sub-section in the guideline or by-law we are interested in, and we can make our comments on that specific article or sub-section.

If every academic staff or most of the academic staff give a comment on any sub-section of a guideline or by-law they are interested in, we can imagine the amount of useful information we can receive to improve the guideline or by-law.

Therefore, I urge all the academic staff to stop being apathetic and distrustful when it comes to providing information to colleagues or to people in the administration and respond to requests for information readily.

ሀኪም ከተገኘ ህመምተኛ ይፈወሳል

በደስታ ተከስተ
ባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ ICT ክፍል

ሀገራችን ኢትዮጵያ በየዘመናቱ በርካታ ተግዳሮቶች ገጥመዋት ያውቃሉ፡፡ ይሁን እንጅ አንድም ጊዜ ቢሆን ለገጠመሟት ተግዳሮቶች እጅ ሰጥታ አታውቅም፡፡ የዚህ ዋነኛ ሚስጢር ህመሟን የሚፈውስ በሀገር ፍቅር መንፈስ የተሞሉ ትጉ ሀኪሞችን ስለምታፈራ ነው፡፡

እነዚህ ሀገር ወዳድ ዜጎች በየዘመናቸው ኢትዮጵያ ስለገጠሟት ችግሮች የመፍትሄ ሃሳቦችን እያመነጨ ከዚያም ባለፈ የህይወት መስዋትነት እየከፈሉ ሀገር እንደ ሀገር ዛሬ የደረሰችበት ደረጃ እንድትደርስ አድርገዋታል፡፡

በእኛ ዘመን ሀገራችን ህመም ገጥሟት ትኖሯለች ህመሞቿም ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ሀይማኖታዊ ተግዳሮቶች ተደራርበው ደቋቁሰዋት ስታቃስት ትሰማለች፡፡ ባለፉት ሦስት ዓሥርት ዓመታት የተዘሩት የጥላቻ ዘር ፍሬ አፍርቶ ለዘረኝነት ለቂምና በቀል ለሁከትና የተዛባ ትርክት ሰለባዎች ሆነዋል፡፡

በየማህበራዊ ሚዲያዎች የሚሰሙት ድምጾች እውነት ኢትዮጵያ እንደ ሀገር አለችን ወይ? ያሰኛል!

በዚህ ወቅት ሃገራችን ዘረኝነት ንተፀይፈው አንድነትን፣መተባበርን፣ፍቅርና ሰላምን የሚሰብኩ የሀገር ፍርቅን የሚዘሩ ትጉ ሀኪሞችን ትፈልጋለች፡፡ ታዲያ እነዚህ ሀኪሞች አነማን ሊሆኑ ይችላሉ? ብለን ልንጠይቅ እንችላለን፡፡ አዎ እነዚህ የሀገር ሀኪሞች ክፉ አስተሳሰብ ያልተጠናወታቸው የፖለቲካ ሀይሎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ የሀገር ሀኪሞች በዘረኝነት ያልተበከሉ ሀገር አስተምራ ለትልቅ ቁምነገር ያበቃቻቸው ቅን አስተሳሰብ ያላቸው ምሁራን ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

እነዚህ የሀገር ሀኪሞች ሀገሬ ስለገጠመች ችግር ትውልዱ ስለገባበት የሞራል ዝቅተት መፍትሄ አለን የሚሉ መካሪና ዘካሪ የሆኑ የሀገር ሽማግሌዎች የእርቅ አምባሳደሮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

እነዚህ የሀገር ሀኪሞች ፍቅርን፣መተሳሰብን የሚሰብኩ፣ በንነትን የሚያስተምሩ፣ እጆቻቸውን ወደ ፈጣሪ ዘርግተው ትውልድን ከፈጣሪው የሚያስታርቁ እውነተኛ የሀይማኖት አባቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

እነዚህ የሀገር ሀኪሞች እውነትን የሚፂፉ ለእውነት የሚኖሩ ሀገራቸውን በትክክል የሚያገለግሉ የተለያዩ የህብረተሰብ አካላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እውነተኛ ትጉ የሀገር ሀኪም ለመሆን መስፈርቱ አንድ ብቻ ነው፡፡ እውነተኛ እና ክልብ የመነጨ የሀገር ፍቅር ነው፡፡

በአንድ የህክምና መስጫ ማዕከል ውስጥ ለመይቸው ብቁ የሆኑና የሠው ህይወት የሚያተርፉ ሀኪሞች እንዳሉ ሁሉ የተወሰኑ ቢሆኑም የሙያ ስነምግባር የጎደላቸውና ስንፍና የተጫናቸው ባለሙያ ተብየዎች ድክመት የህይወት እልፈት አለያም ተጨማሪ ህመም የሚሠጡ እንዳሉ ይታወቃል፡፡

ወደ ገፅ 6 ዞሯል

ይህ አምድ በዋነኛነት የተማሪዎች ድምፅ እና ተማሪነትን የሚመለከቱ ዕሁፎች ይቀርብበታል

ደቀመዛሙርት

የመሪ ተከታይ አይነቶች

በፕ/ር የሺጌታ ገላው
ከህክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ

በአመራር ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጣቸው ዓብይ ጉዳዮች አንዱ የመሪና የተከታዮች መስተጋብር ነዉ፡፡ ይህ እዉነታ በዓለማዊም ሆነ በመንፈሳዊ ተቋማት ተልዕኮን ከማሳካት አንፃር እጅግ ወሳኝ ነዉ፡፡ ይህን መስተጋብር በጥልቀትና በስፋት ለማወቅ የዘርፉ ተመራማሪዎችና ልሂቃን እ.ኤ.አ ከ1960ዎች ጀምሮ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በማድረግም ላይ ናቸው፡፡

ፈጣሪያችን በዚች ምድር በቆየበት ጊዜ ከተከታዮቹ ጋር የነበረው ግንኙነትና ተከታዮቹ ያሳዩት የነበረውን ባህርያት ለዘርፉ ልሂቃን ጥሩ መነሻ ሆኗል ብየ አምናለሁ፡፡ በስራ አመራር ትምህርት ዉስጥ ለሚጠቀሱ ታዋቂ የስኬት መስተጋብራዊ ቀመሮችም ቅዱስ መጽሐፍና ቅዱስ ቁርዓን መነሻ እንደሆኑ መገመት አይከብድም፡፡

የተለያዩ የምልከታና የአመራር ዘዴዎችን/ንድፈሐሳቦችን/ በመጠቀም የተከታይ አይነቶችን ወይንም ዋና ዋና ባሕሪያቸውን ከሶስት እስከ ሰባት በሚሆኑ መደቦች ከፍሎ ማየት እንደሚቻል ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡

አንድ ተከታይ በዉጫዊ ምክንያቶች፣ በአስተሳሰብ ለዉጥ፣ በትምህርትና ስልጠና፣ በልምድ ልዉዉጥ፣ በመሪው የአመራር ዘይቤ/ተግባር/፣ወዘተ ከአንዱ ምድብ (አይነት) ወደ ሌላ ምድብ ሊገባ ይችላል፡፡የሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ምሁር ባርባራ ኪለርማን እ.ኤ.አ በ2007 ዓ.ም 'መሪዎች ስለተከታዮቻቸው ማወቅ ያለባቸው ጉዳዮች' በሚለው ጽሑፋቸው ተከታዮችን በአምስት ምድብ በመክፈል ሰፊ ገለፃ አድርገዋል፡፡

እ.ኤ.አ በ2014 ዓ.ም ካናዳዊቷ ብሪጀት ሀያስንፍ የተባሉት ተመራማሪ በጥናታቸው የመሪ ተከታዮችን በሰባት ከፍለዉ ያዩበት መንገድ የተሻለና ሁሉን አካታች ሆኖ ስላገኘሁት የግል ምልከታ እና ተሞክሮ በማካተት ዝርዝሩን እንደሚከተለው አቅርቤአለሁ፡፡

ሰባቱ የተከታይ አይነቶች፡-

1. ታማኝ_ደጋፊ

እነዚህ ተከታዮች መሪያቸውን ከልባቸዉ የሚደግፉ፣ የሚወዱና የሚያደንቁ ደቀ መዝሙሮች ናቸው፡፡ የመሪያቸው ተልዕኮ እንዲሳካና ተቋማቸው ዉጤታማ እንዲሆን እጅግ የሚተጉ ናቸው፡፡ መሪያቸዉም በእነዚህ ሰዎች ይተማመናል፤ አብዛኛዉን ስራም በእነዚህ ሰዎች በኩል ያስፈጽማል፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ ተከታዮች የመሪያቸዉ ፍፁም አድናቂ ከመሆናቸው የተነሳ በስራ ሂደት የሚታዩ ስህተቶችን መጠቆም/ማመላከት/ ስለማይችሉ መሪያቸዉ በሚያገኘው እንከን የለሽ ግብረ መልስ አማካኝነት አልፎ አልፎ ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ሊያመራ ስለሚችል ግቡን እንዳየሳካ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

2.እዉነተኛ_(ምክንያታዊ)

እነዚህ ተከታዮች የተቋማቸዉን ነባራዉ ሁኔታና የመሪያቸዉን አፈፃፀም በመርህ፣ በእዉነትና በአመክንዮ እየገመገሙ መልካም ስራ እስከተሰራ ድረስ መሪያቸዉን መቶ በመቶ የሚደግፉ ናቸው፡፡

በስራ ሂደት የሚታዩ ስህተቶች/ክፍተቶች/ ካሉ ደግሞ በይፋ ገንቢ አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ ለተቋማቸው ዉጤታማ መሆን የተሻለ መንገድ አለ ብለው ሲያምኑ መሪያቸዉን በአመክንዮ ይሞግታሉ፡፡ ከተቋም ግንባታ አንፃር የእነዚህ ተከታዮች አስተዋጽዖ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ መሪዎች በቅርበት ሊይዟቸው ይገባል፡፡ አልፎ አልፎ በመሪውና በእውነተኛ ተከታዮች መካከል ሰፊ የእሳቤ ወይም የልምድ ልዩነት ሲኖር የመሪዉ አዳዲስ ፈጠራዎች/የአመራር ዘዴዎች እንዳይተገበሩ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

3. ወላዋይ_(ጥቅመኛ)

እነዚህ ተከታዮች ዋናው ትኩረታቸው የራሳቸዉን ጥቅም ማስጠበቅ ስለሆነ ስልጣን/ጉልበት/ ካለው አካል ጋር ከመጣበቅ ወደኋላ አይሉም፡፡ በመሪያቸው መወደስ፣ መመስገን፣ መሸለም፣ ወዘተ የደስታቸው ምንጭ ነዉ፡፡ መሪያቸውን ለግላዊ ስኬታቸው መሰላል አድርገው ይቆጥራሉ፡፡

የተሻለ ጥቅም የሚያስገኝላቸው አካል ካገኙ ወይም የሚያገኙ ከመሰላቸው ደግሞ በብርሃን ፍጥነት ዐይናቸዉን በጨው አጥበው ዘወር የሚሉ፣ ኃፍረት (ይሉኝታ) የሚባል ነገር የማያዉቁ ተከታዮች ናቸው፡፡ ይህን ዓይነት ባህርይ የተላበሱ ሰዎች በሁሉም የስራ ዘርፎች/ተቋማት ቢኖሩም የፖለቲካዉ ዓለም የዘወትር ነፀብራቅ ናቸው፡፡

በንግድ ስራ በተሰማሩና በማሕበረሰብ አንቂዎችም ዘንድ ይታያሉ፡፡ መሪዎች እነዚህን ተከታዮች በተቻለ መጠን ለይተዉ ማወቅ ከቻሉ ለተቋም ግንባታ ሊጠቀመባቸው ይችላሉ፡፡ ከሽልማት ጋር የተቆራኙ ፍፁማዊ ለውጦችን በፍጥነት ከመተግበር አንፃር ሚናቸው የጎላ ነዉ፡፡ ጥቅማቸው ሳይከበር ሲቀር ደግሞ የተቃዋሚ ተከታዮችን ጎራ በቀላሉና በፍጥነት ሊቀላቀሉ ይችላሉ፡፡

4.አሽቃባጭ(ብልጣብልጥ)

እነዚህ ተከታዮች 'ንጉሡ ሺ ዓመት ይንገሡ'፣ 'ስማይ አይታረስ ንጉሥ አይከስስ'፣የሚሉ ዓይነት ሰዎች ናቸው፡፡ ከመሪያቸው የመጣን ነገር ቢያምኑበትም ባያምኑበትም፣ ትክክል ይሁንም አይሁንም እሺ በማለት የተካኑ አሽቃባጭ ተከታዮች ናቸው፡፡ 'ፀሀይ በምዕራብ ትወጣለች' ቢባሉ ጌታዬ ልክ ብለዋል የሚሉ አይነት ሰዎች ናቸው፡፡ ለራሳቸው ያልታመኑና አለቃቸዉን ለመገሰፅ ቅንጣት የማይደፍሩ አስመሳዮች በመሆናቸው ከፍተኛ ማሳሳለል ለሚጠይቁና ከበድ ያለ ዉሳኔ ለሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች አጋዥ አይሆኑም፡፡ መሪዎች ሳያውቁ ከበድ ባሉ ጉዳዮች ላይ እነዚህን ተከታዮች ሲያማክሩ/ሲያሳትፉ/ ከፍተኛ ጥንቃቄ ካለደረጉ የተሳሳተና አደገኛ ዉሳኔ እንዲወስኑ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ተቋሙን ለውድቀት ሊዳርጉት ይችላሉ፡፡ የመሪዎች ታላቁ ፈተናም እነዚህንና መሰል ተከታዮችን ከታማኝ ደጋፊዎች የመለየቱ ስራ ነዉ፡፡

5. ተመልካች(ጉልት)

እነዚህ ተከታዮች ስራ የሚሰሩት ለደሞወዝ/ለክፍያ/ ብቻ ስለሆነ በመሪያቸውና በተቋማቸው ጉዳይ ዉስጥ በፍፁም አይገቡም፡፡ መሪያቸዉን አይቃወሙም፣ አይደግፉም፡፡ ድምፀ-ተዓቅቦ የዘወትር መገለጫቸው ነዉ፡፡ 'እናቴን ያገባ ሁሉም አባቴ ነዉ' ባዮች፣ ስራሳቸው ተቆጥሮ የተሰጣቸውን ስራ ከመከወን ዉጭ በተቋማቸው ዉስጥ ምንም አይነት ንቁ ተሳትፎ አያደርጉም፡፡ ስለሆነም 'ጉልት' ተከታዮች የሚል ስያሜ ሰጥቻቸዋለሁ፡፡

6. ከዳተኛ_(ክሃዲ)

እነዚህ ተከታዮች መሪያቸዉን ያለበቂ ምክንያት በስዉር አምርረው የሚጠሉና ስኬታማ እንዳይሆን ቀን ከሌሊት ሴራ የሚሸርቡ ሰዎች ናቸው፡፡ ስለመሪያቸው ክፍተኛ የሆነ የጥላቻ ስሜት ያለባቸው ተከታዮች ናቸው፡፡ ተቀርቋሪና ታማኝ መስለው ከመጋረጃው በስተጀርባ ደግሞ ለመሪያቸው መቃብር ይቆፍራሉ፡፡

በሌላ አገላለፅ 'የጭቃ እሾህ' ናቸው፡፡ ተሳካም አልተሳካም መሪያቸዉንና ተቋማቸዉን አሳልፈው ለመስጠት እጅግ ይተጋሉ፡፡ መሪያቸውን ለማድማትና ለማቁሰል እንዲሁም ክስተት የሆኑ ለተቋም አስተጋሪና ፈታኝ የሆኑ አጋጣሚዎችን ካገኙ መሪያቸው ብቃት እንደሌለው ዐይኔን ግንባር ያርገው ብለው በሐሰት ለመመስከር የሚቀድማቸው ተከታይ የለም፡፡ በቅዱስ መጽሐፍ "እንጀራዬን የበላ ተረከዙን አነሳብኝ" ተብሎ እንደተጻፈው መሪያቸው የቱንም ያህል መልካም ቢሆን ጥፋትን ይሰንቃሉ፡፡

በአጠቃላይ ምግባራቸዉ ክርስርቶስን በሰላሣ ዲናር አሳልፎ ከሰጠው ከአስቆረቱ ይሁዳ ጋር ስለሚመሳሰል ይሁዳዎች ይባላሉ፡፡ እነዚህ ተከታዮች የተመሰከረላቸውና የተካኑከያንያን/ተዋንያን/ በመሆናቸው ኅብዝና አስተዋይ መሪዎች ሳይቀሩ እነዚህን ሰዎች በአጭር ጊዜ ለመለየትና በቅርብ ርቀት ለመከታተልና የሚፈጥሩትን ጫና ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ ሊችገሩ ይችላሉ፡፡

ጀማሪ መሪዎች የእነዚህን ሰዎች ተንኮል አስቀድሞ ማወቅና በቂና አዋጭ ተግባራዊ ምላሽ መስጠት ላይ ዉሱንነት ስላለባቸው በቶሎ እጅ ሊሰጡና ተገዢዉን የመሪነት ሚና ሳይወጡ ሊቀሩ ይችላሉ፡፡ ሳይደግስ አይጣላም እንዲሉ የእነዚህ ተከታዮች ቁጥር እጅግ አናሳ ነዉ፡፡

7. ነቃፊ(ተቃዋሚ)

እነዚህ ተከታዮች ደግሞ መደበኛ ስራቸው የመሪያቸውን ርዕይ፣ ተልዕኮ፣ የአመራር ስልቶች፣ ፖሊሲዎች፣ የስራ ዉጤቶች ወዘተ መንቀፍና መቃወም ነዉ፡፡ ካልነቀፉ መንግሥት ሰማይን የሚወርስ አይመስላቸዉም፡፡

በመሪያቸው ወይም በተቋማቸው ተገቢዉን ክብር ወይም ሽልማት አላገኘንም ብለው የሚያስቡ ወይም ግላዊ ትልማቸው የተሰናከለባቸው በመሆናቸው የተቃዉሞ ድምፅ በይፋ በማሰማትና አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደር በራሳቸው እሳቤ ይገባናል የሚሉትን ክብርና ዝና ለማስመለስ ደፋ ቀና ይላሉ፡፡ ለንግሥና መታጨት የማይፈልጉ (ወይም የማይታጨ)፣ የሚፈልጉትን ለማንገስ ግን ብዙኃኑን ለማንቀሳቀስ የሚታትሩ ተከታዮች ናቸው፡፡

የተቋም ዉክልና ሳይሰጣቸው ከመሪያቸው በተቃራኒ ጎራ በመሰለፍ እራሳቸውን የተቋሙ አጋፋሪ ወይም ጠበቃ አድርገው ይቀርባሉ፡፡ ወደ ተቋማቸው አዲስ ሰራተኛ ወይም እንግዳ ሲመጣ ፈጥነዉ አቀባበል በማድረግና የተቋማቸውን ገጽታ በማጠልሸትና ጨለምተኛ አስተሳሰብንና የተበዳይነት መንፈስን በማስረፅ መሰል ተከታይ ለማፍራት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

እነዚህ ሰዎች በባህርያቸው መልካቸዉን ስለማይቀያይሩና ተቃዋሚ መሆናቸውን በይፋ ስለሚያሳውቁና ከእነርሱ የሚጠበቀውም ስለሚታወቅ ለመሪዎችና ለሌሎች ተከታዮች ክፍድ ፈተና አይሆኑም፡፡ ሆኖም ግን በመሪዉና በሌሎች ተከታዮች ያልታዩ ምልከታዎችን ለማየት ሊያግዙ ይችላሉ፡፡

ፕ/ር ዶናልድ ሎምባርዲ አዳዲስ የጤና አመራሮችን ለማገዝ በ2001 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) በጻፉት መጽሐፋቸው እንደተገለው ከተከታዮች መካከል ክክብ ሰራተኞች ከ15-20%፣ አጥጋቢ/ መካከለኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ከ60-70%፣ ለተቋማዊ ስኬት ሚና የሌላቸው ደግሞ ከ10-15% እንደሆኑ አውቆ መስተጋብሩን ከዚህ ስሌት አንፃር መቃኘት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

መሪነት_ሆነ ተመሪነት ቀላል ነው ብየ ባልገምትም መሪዎች የተከታዮቻቸውን ዓይነት ጠንቅቀው ማወቅና ተቋምን ያስቀደመ አካባቢያዊ መስተጋብር መፍጠር ይገባቸዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር በአንድ ምድብ ዉስጥ የሚገኙ ተከታዮችን ብዛትና ያላቸውን ተቋማዊ ሚና በተቻለ መጠን ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርሁት ይህ ክፍፍል በጥቅሉ የመሪ ተከታዮችን ዝርዝር ባሕርያት ለማሳየት ቢረዳም አንድ ሰው በሂደታዊ/ምክንያታዊ/ ለዉጦች ከአንዱ ምድብ (አይነት) ወደ ሌላ አይነት ተከታይ ሊቀየር/ ሊለወጥ/ እንደሚችል በማወቅ የተከታዮችን ወቅታዊ ምድብ በማጤን መስተጋብርንና ተግባቦትን በቢዜው ማስተካከል የግድ ይላል፡፡

ጤንነት

ይህ አምድ የተለያዩ ጤና ነክ ጉዳዮችና ጤንነትን የተመለከቱ ምክረ ሃሳቦች ይቀርብበታል

የጉበት በሽታ አምጭ ቫይረስ አይነቶች፤መተላለፊያ እና መከላከያ መንገዶቻቸዉ

ዮሐንስ ዘነበ
በተላላፊና ትሮፒካል በሽታዎች ረ/ፕ
ክህክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ

የጉበት ተግባራት

ጉበት ዋነኛ ከሚባሉት የሰዉነታችን ክፍሎች ዉስጥ አንዱና በመጠን ትልቁ ነዉ፡፡ ጉበት ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡
ከነዚህም ዉስጥ፡-
ሰዉነታችንን ሊጎዱ የሚችሉ መርዛማንጥረ-ነገሮችን የመርዛማነትባህሪያቸዉን በማሳጣት የሰዉነታችንን ጤንነት ይጠብቃል፡፡

ለሰዉነታችን ጠቃሚ የሆኑ ንጥረ-ነገሮችን በማምረት ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ያደርጋል፡፡ ለምግብ መፈጨት አስፈላጊ የሆነ ሃሞት (Bile)የሚባል ንጥረ-ነገር ያመርታል፡፡

በሰዉነታችን ዉስጥ ትርፍ የሆነዉን ምግብ (ግሉኮስን) ግላይኮጅን ወደሚባል የምግብ ክምችት በመቀየር እንዲከማች ያደርጋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወደ ግሉኮስ በመቀየር ጥቅም ላይ እንዲዉል ያደርጋል፡፡

የጉበት ጥቅም ከፍተኛ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉበት በተለያዩ ነገሮች ሊጎዳ ይችላል፡፡ ጉበትን ሊጎዱ ከሚችሉት ነገሮች ዉስጥ ዋናዋናወቹ የሚከተሉት ናቸዉ፡-

- የጉበት በሽታ አምጭ ተዋህሲያን/ቫይረሶች (Hepatis Viruses) ፤
- የአልኮል መጠጥ፤
- መድሃኒት ለረጅም ጊዜ መዉሰድ፤
- አላስፈላጊ በሆነ የሰዉነታችን ግብረ-መልስ (Autoimmunity) እና ወዘተ በመሳሰሉት ነገሮች ሊጎዳ ይችላል፡፡

የጉበት በሽታ አምጭ ተዋህሲያን ቫይረሶች

የጉበት በሽታ በተለምዶ የወፍ በሽታ እየተባለ የሚጠራ የበሽታ ዓይነት ሲሆን፡ የጉበት በሽታ አምጭ ተዋህሲያን/ቫይረሶች (Hepatitis Viruses) የጉበት በሽታን ሊያስከትሉ ከሚችሉ ምክኒያቶች ዉስጥ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡ ሄፓታይተስ ቫይረሶች ስያሜያቸዉን ያገኙት በእንግሊዘኛ ሄፓቶሳይት (Hepatocyte) ተብለዉ ከሚታወቁት የጉበት ህዋሳት (Cells) ሲሆን እነዚህ የቫይረስ አይነቶች እስካሁን ባለዉ መረጃ መሰረት ከጉበት ህዋሳት ዉጭ በሌላ የሰዉነት ክፍል ላይ መራባትም ሆነ በሽታ የማስከተል አቅማቸዉ ደካማ ነዉ፡፡ በጉበት ካንሰር ከተያዙት መቶ ሰዎች መካከል ሰማንያ የሚሆኑት ሰዎች የበሽታቸዉ መንስኤ የጉበት በሽታ አምጭ ቫይረሶች እንደሆኑ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡

በጉበት በሽታ አምጭ ቫይረሶች (Hepatitis Viruses) የተያዘዉ ማንኛዉም ሰዉ ጉበቱን በይበልጥ እንዲጎዳና ከጥቅም ዉጭ እንዲሆን ከሚያደርጉት ተጓዳኝና አባባሽ ነገሮች ዉስጥ፡-አልኮል መጠጣት፤መድሃኒት አዘዉትሮ መዉሰድ፤ለተለያዩ ኬሚካሎች መጋለጥና ከልክ ያለፈ ዉፍረት ዋናዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

ለጉበት በሽታ መንስኤ ናቸዉ ተብለዉ በዋናነት ከተለዩት የቫይረስ አይነቶች ዉስጥ ሄፓታይተስ-ኤ(HAV)፡ሄፓታይተስ-ቢ (HBV)፤ሄፓታይተስ-ሲ(BCV)፤ሄፓታይተስ-ዲ(HDV)እና ሄፓታይተስ-ኢ(HEV)ይጠቀሳሉ፡፡

በእነዚህ የቫይረስ ዓይነቶች አማካኝነት የሚመጣዉ የጉበት በሽታ እንደየጉዳት ደረጃቸዉ የተለያዩ ናቸዉ፡፡ ከእነዚህም ዉስጥ፡- አጣዳፊ የጉበት በሽታ (Acute hepatitis)፤ የቆየ የጉበት በሽታ (Chronic hepatitis)፤ የጉበት ለምዕና (Scars) የጉበት ካንሰር (Liver cancer) በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

ሄፓታይተስ-ኤ (Hepatitis A)

ሄፓታይተስ-ኤ በክትባት መከላከል የምንችለዉ የበሽታ አይነት ሲሆን የሚከሰተዉም ሄፓታይተስ-ኤ ቫይረስ (Hepatitis A virus) በሚባል የቫይረስ ዓይነት ነዉ፡፡

ይህ የቫይረስ አይነት ቫይረሱ ካለባቸዉ ሰዎች ወደ ጤነኛ ሰወች የሚተላለፈዉ ከበሽተኛዉ በሚወጣዉ አይነምድር አማካኝነት የተበከለ ምግብ በመብላት ወይም የተበከለዉን መጠጥ በመጠጣት ሲሆን እስካሁን ባለዉ መረጃ መሰረት ፍቱን መድሃኒት የለወም፡፡ በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ከማንኛዉም የአልኮል መጠጦች መቆጠብ እንደሚኖርባቸዉ በባለሞያወች ይመከራል፡፡

አንድ በሄፓታይተስ-ኤ ቫይረስ የተጠቃ ሰዉ እንደ አልኮል ከመሰሉ አባባሽ ነገሮች ከተቆጠበ ብዙዉን ጊዜ በሽታዉ ያለምንም መድሃኒት ሊድን ይችላል፡፡
በቫይረሱ ላለመጠቃት የሚከተሉትን የመከላከያ መንገዶች መጠቀም ይገባል፡-

- ሁልጊዜ ከምግብ በፊት አጅን በዉሃና በሳሙና መታጠብ
- ሽንት ቤት ከተጠቀሙ በኋላ አጅን በዉሃና በሳሙና መታጠብ
- በተቻለ መጠን፤ ማንኛዉንም ምግብ አብስሎ መመገብ
- ለመጠጥነት የምንጠቀመዉን ዋሃ ንፁኅ ከሆኑ የዉሃ ምንጮች መጠቀም፤ የተቀዳዉን ዉሃ በንጽህና መያዝ፤ አጠራጣሪ ከሆነ የዉሃ ምንጭ የተቀዳን ዉሃ አፍልቶ በማቀዝቀዝ መጠቀም
- በጥሬዉ የሚበሉ አትክልትና ፍራፍሬወችን በንጹህ ዉሃ በደንብ አጥቦ መመገብ

•የሄፓታይተስ-ኤ ክትባት መዉሰድ

ሄፓታይተስ-ቢ((Hepatitis B)

ሄፓታይተስ-ቢ ቫይረስ በመባል የሚጠራዉ የቫይረስ አይነት ጉበትን ከሚጎዱ የቫይረስ አይነቶች ዉስጥ የመጀመሪያዉን ደረጃ የሚይዝ ሲሆን በሃገራችን በከፍተኛ ደረጃ በሽታዉ እየተስፋፋ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህ ቫይረስ ከህመምተኛዉ ሰዉ ወደ ጤነኛ ሰዉ ከሚተላለፍባቸዉ መንገዶች ዉስጥ ዋነኛዉ በደም ንክኪ ሲሆን በዚህ መንገድ የመተላለፍ እድሉ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዘርፉ በተጠኑ ጥናቶች የመተላለፊያ መንገድ ናቸዉ ተብለዉ ከተለዩት ዉስጥ፡ የደም ልገሳ፤ ስለታማ ነገሮችን በጋራ መጠቀም፤ በተበከለ መርፌ መወጋት፤ የሰዉነት ንቅሳትና ጥርስ መቦረሻ መገልገያወችን በጋራ መጠቀም ይገኙበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጥንቃቄ የጎደለዉ ግብረ-ስጋ ግንኙነት እና በቫይረሱ ከተያዘች እናት ወደ ፅንስ (ልጅ) ሊተላለፍ ይችላል፡፡

ሄፓታይተስ ቢ ቫይረስ ፍቱን መድሃኒት ባይኖረዉም የመከላከያ ክትባት ግን አለዉ፡፡ መከላከያ መንገዶችም ከላይ ከተጠቀሱት አጋላጭ ነገሮች እራስን መጠበቅና ክትባቱን መዉሰድ ተገቢ ነዉ፡፡

ሄፓታይተስ-ሲ (Hepatitis C)



ሄፓታይተስ-ሲ ቫይረስ የሚባለዉ የቫይረስ አይነት ደግሞ እንደሄፓታይተስ-ቢ ቫይረስ ሁሉ የጉበት በሽታን በማስከተልና ጉበትን በከፍተኛ ደረጃ በመጉዳት የሚታወቅ የቫይረስ አይነት ነዉ፡፡

በሃገራችን ከሄፓታይተስ ቢ ቫይረስ በመቀጠል እየተስፋፋ ያለ የቫይረስ አይነት ነዉ፡፡ ይህ የቫይረስ ዓይነት ከበሽተኛዉ ሰዉ ወደጤነኛ ሰዉ የሚተላለፈዉ በደም ንክኪ ሲሆን በተወሰነ መልኩም ልቅ በሆነ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ሊተላለፍ እንደሚችል ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ሄፓታይተስ ሲ ቫይረስ መድሃኒት

ወደ ገፅ 11 ዞሯል

ኪነጥበብ እና ባህል

ልክ አይደለም!!

በሃሩት አድማሱ
አማርኛ ቋንቋ እና ስነፅሁፍ ትት ክፍል ባ/ዳር ዩኒቨርስቲ

ከተለመደው መርበትበት እና መንጎዳጎድ በኋላ አንድ ካፌ ቁርስ ለመብላት ገብቻለሁ፡፡

ጓደኛየን "ቁርስ እንብላ" አልኳት፤ "በልቻለሁ፡፡ ቡና ብቻ ነው የምፈልገው" አለችኝ፡፡

"ተይ ክሽን ተደርጎ የተሰራ ምግብ ነው ብትበይ ይሻልሻል፣?"ራሴ የሰራሁት ምግብ ስለሆነ ነው አልኳት፡፡ "ኧረ ቁርሴን ባሌ የሰራውን ክሽን ያለ ዶሮ ነው የበላሁት፡፡" አለችኝ፡፡

የዚህ ጊዜ ጠረጴዛ የተጋራናቸው ሁለት ወንዶች አላስቻላቸውም፡፡
"እድሰኛ ነሽ ባልሽ ዶሮ ሰርቶ ካበላ፡፡"
"እንዴት ለምንድን ነው እድሰኛ የምባለው እኔስ ሰርቼ አበላው አይደል እንዴ;?" አለች፡፡

"የለም በስሙ ሁልጊዜ እየሄድሽ ቤተክርስቲያን መስገድ ይገባሻል፡፡"

ጓደኛየ ሳቅ አለችና "ለምንድን ነው የምሰግደው; ምን አዲስ ነገር ነው እንዴ;?"

"የለም በእኛ ሀገር ባህል ወንድ ሰርቶ ሚስቱን አያበላም፡፡" አላት፡፡
"ለመሆኑ ብሔሩ ምንድን ነው;"
የወቅቱ ጥያቄ ቀጠለ
"ብሔር የለውም፡፡"
"እንዴት ይሆናል?"
"በብሔሩ ይሰራል አይሰራም ልትል ፈልገህ ነው?"

"አዎ ለምሳሌ" ብሎ ጠቀሰ... የወሬው አዝማሚያ አልተመቸኝም ጭራሽ "ዶሮ መስራት ብችል ሚስት አላገባም" አለ፡፡

የዚህን ጊዜ ጣልቃ መግባት ግድ ሆነብኝ፡፡ "ወጥ ለማሰራት ነው እንዴ የምታገባው?" ጥያቄ አቀረብኩ፡፡ ቀጠልኩ "እንደዚያ ከሆነ እኮ ሰራተኛ መቅጠር ይበቃል፡፡"

"እንደዚያ ለማለት ፈልጌ አይደለም፡፡ ካስፈለገም ደግሞ አዎ ሚስት ሰራተኛ ናት ለባሏ፤ ባልም ለሚስቱ ሰራተኛ ነው፡፡"

"ይልቅ አንቺ በጣም እድሰኛ ነሽ እና ብሔሩ ምንድን ነው;?" አለ ወደ እሷ ፊቱን መልሶ፡፡ ወይ ጉድ! "ኢትዮጵያዊ አይደለም፡፡"ገላገልኳቸው፡፡

"አዎ እንደዚያ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ እንዳህ አይሰራም፡፡" እኔን ለምሳሌ ኩሽና ግባ ከምትይኝ የፈለገሽን ብታገርኝ ይቀለኛል፡፡ ለምን; ያስጠላኛል፡፡"

ራሱ ጠይቆ ራሱ መለሰ፡፡ "ያስጠላኛል?" "ሴት የሚያስጠላ ስራ እንድትሰራ የተፈረደባት ስለምንድን ነው; ሁሉም ሰርተው ውለው መጥተው ሴት ወደ ኩሽና ወንድ ወደ ቴሌቪዥን ወይም መኝታ መሆን የለበትም፡፡" ንግግሬን አቋርጦ፤

"ወጥ ለማሰራት ነው ወይ የምታገባው ላልሺኝ; ኧረ ሚስት የማገባው ወጥ ለማሰራት አይደለም የቀልዴን ነው፡፡" "በል አታስቀኝ! የለም እዚህ ሀገርማ ሚስት ተገባ ማለት የቤትን ስራ የምትከውን ሴት አገኘህ ተገላገልክ ማለት ነው፡፡"

"ብቻህን እያለህ ቀልጠፍ አድርገህ ስትሰራ የነበረውን ሚስት አገባሁ በሚል ሁሉን ለሷ እርግፍ አድርጎ መተው የተለመደ የኢትዮጵያዊ ወንዶች ልማድ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ አስተሳሰብ ነው መቅረት ያለበት፡፡ ይሄ ከጭቆና ይቆጠራል፡፡ የሴቶች ጭቆና መቅረት አለበት፡፡"

"ጓደኛየ እዚህ ጋ ቀጠል አድርጋ አዎ ሴትም ወንድን ተሳስበው መስራት አለባቸው፡፡ እኩል ሰርተው ገብተው የኩሽናው ስራ ሰሷ ብቻ መተው የለበትም፡፡"

"ወንዶች በባህላችን የኩሽና ስራ አንሰራም፡፡ የገጠር ወንድ ውጭ ውጪውን ሲሰራ የከተማው ወንድ ግን የኩሽናው ስራ በሰራተኛ ስለሚሻፈን የኩሽና ስራ መስራት አያውቅም፡፡" አለ አንደኛው፡፡

ይህ ዓይነቱ ተግባር (የቤት ውስጥ ስራ) በገጠርም ሆነ በከተማ በሴቶች ላይ ጫና ያሳርፋል፡፡ አንድ አዋር ልቦለድ ለአብነት አነሳሁ፡፡ በታሪኩ ውስጥ ያለችው የገጠር ሴት በቁርባን ያገባች እና ባሏን ለመርዳት ቀን ቀን እርሻ የምትውል፡፡ ማታ ማታ እሱ እቤቱ እግሩን ዘርግቶ ሲያርፍ እሷ ገብታ ምግብ ሰርታ የምታበላና እግሩን የምታጥብ ናት፡፡

ምን አለፋህ ከከተማ እስከ ገጠር ሴት ተበድላለች፡፡ ከጉልበት እስከ ስነልቦና ድረስ ጫና ይደረግባታል፡ ያለ ምስጋናና ፍቅር የሰራችውን በመንቀፍ እንዳትረክ ትደረጋለች፡፡

ካወራሁት አንዱን ነቅሶ አውጥቶ፤ "እግር ማጠብ መበደል ነው፡፡"

"እኩል ስራ ተሰርቶ ከተመጣ እኩል ቤት ውስጥ ያለውንም ስራ መጋራት ያስፈልጋል፡፡ አንዱ ተቀማጭ ሌላው አላጋጭ መሆን የለበትም፡፡"

ወደ ታሪኩ ስመለስ እና ያቺ ሴት ለእግድነት መጥቶ እቤታቸው ባደረው የባሏ ጓደኛ ባሏ በሌለበት ተደፈረች፡፡ በዚህም እምነቱን አጎደፍኩ ብላ እራሷን አጠፋች፡፡
"እዚህ ላይ ተሳሳትሽ ሀይማኖቷ ምንም አላደረጋትም፡፡"

"ሀይማኖቷ ምን አደረጋት ትልኩኝ; በዚያ ላይ የአዋር ልቦለድ ታሪክ ነው እያወራሁ ያለሁት፡፡"

"እንደማይሽ ከሆነ መብሰል ይቀርሻል፡፡"

የባሰ አለ... አለ ያገሬ ሰው!

ሀሳቤን መሞገት ሲያቅተው የቃላት ትንኮሳውን እኔ ላይ መወርወር ጀመረ፡፡ እሱ ወንድ ስለሆነ የፈለገውን የመናገር መብት አለው፡፡ ውስጤ ተበሳጨ፡፡

"አዎ ሙሉ እውቀት አለኝ አልልም፡፡

ወደ ገፅ 12 ዞሯል

የጉበት በሽታ...

ከገፅ 10 የቀጠለ

ጥርስ መቦረሻ መገልገያወችን በጋራ መጠቀም ይገኙበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጥንቃቄ የጎደለዉ ግብረ-ስጋ ግንኙነት እና በቫይረሱ ከተያዘች እናት ወደ ፅንስ ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ሄፓታይተስ ቢ ቫይረስ ፍቱን መድሃኒት ባይኖረዉም የመከላከያ ክትባት ግን አለዉ፡፡ መከላከያ መንገዶችም ከላይ ከተጠቀሱት አጋላጭ ነገሮች እራስን መጠበቅና ክትባቱን መዉሰድ ተገቢ ነዉ፡፡

ሄፓታይተስ-ሲ(Hepatitis C)

ሄፓታይተስ-ሲቫይረስ የሚባለዉ የቫይረስ አይነትደግሞ እንደሄፓታይተስ-ቢ ቫይረስ ሁሉ የጉበት በሽታን በማስከተልና ጉበትን በከፍተኛ ደረጃ በመጉዳት የሚታወቅ የቫይረስ አይነት ነዉ፡፡ በሃገራችን ከሄፓታይተስ ቢ ቫይረስ በመቀጠል እየተስፋፋ ያለ የቫይረስ አይነት ነዉ፡፡ ይህ የቫይረስ ዓይነት ከበሽተኛዉ ሰዉ ወደጤነኛ ሰዉ የሚተላለፈዉ በደም ንክኪ ሲሆን በተወሰነ መልኩም ልቅ በሆነ የግብረ-ስጋ ግንኙነት ሊተላለፍ እንደሚችል ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ሄፓታይተስ ሲ ቫይረስ መድሃኒት ያለዉ ሲሆን፤ ክትባቱ ግን እስካሁን ድረስ ያልተገኘለትና በምርምር ላይ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

የቫይረሱ የመከላከያ መንገዶች ከሄፓቲቲስ ቢ ቫይረስ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን ሌሎች እንደ አልኮል ካሉ አባባሽ ነገሮች መቆጠብ ቫይረሱ በጉበት ላይ የሚያደርሰዉን ጉዳት መቀነስ እንደሚቻል የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ፡፡

ሄፓታይተስ-ዲ (Hepatitis D)

ሄፓታይተስ-ዲ ቫይረስ የሚባለዉ የቫይረስ አይነት እምብዛም የማይከሰት የቫይረስ አይነት ሲሆን የሚያጠቃቸዉ ሰወች በሄፓታይተስ-ቢ የተያዙትን ሰወች ብቻ ነዉ፡፡ ስለሆነም ሄፓታይተስ-ቢ ያለባቸዉ ሰዎች በሄፓታይተስ-ዲ ቫይረስ የመጠቃት እድላቸዉ ከፍተኛ ስለሆነ ለዚህ ቫይረስ ምርመራ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ የሄፓታይተስ-ዲቫይረስ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶችም ከሄፓታይተስ-ቢ ቫይረስ ጋር ተመሳሳይነት አለዉ፡፡

ሄፓታይተስ-ኢ (Hepatitis E)

ሄፓታይተስ-ኢ ቫይረስ ዉሃ ወለድ በሽታ አምጭ ከሚባሉት የቫይረስ አይነቶች አንዱ ሲሆን ዋናዉ የመተላለፊያ መንገድ በቫይረሱ ከተያዘዉ ሰዉ በሚወጣ አይነምድር የተበከለ ዉሃ በመጠጣት ወይም ምግብ በመብላት ነዉ፡፡ ይህ ቫይረስ አብዛኛዉን ጊዜ በነፍሰጡር እናቶች ላይ መጠኑ ከፍ ብሎ ይታያል፡፡ በተለያዩ የሃገራችን ክፍሎች የተጠኑ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፡ የቫይረሱ መጠን በከፍተኛ ደረጃ አንዳለና የመተላለፊያ መንገዱም ሲታይ ከንፅህና ጉድለት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት እንዳለዉ ነዉ፡፡ የመከላከያ መንገዶች ከሄፓታይተስ-ኤ ቫይረስ ጋር ተመሳሳይነት አለዉ፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሄፓታይተስ-ኤ (HAV)፡ እና ሄፓታይተስ-ኢ (HEV) የሚባሉት የቫይረስ አይነቶች በተበከለ ምግብና ዉሃ አማካኝነት የሚተላለፉ የቫይረስ አይነቶች ሲሆኑ፡ ሄፓታይተስ-ቢ (HBV)፤ሄፓታይተስ-ሲ (BCV) እና ሄፓታይተስ-ዲ(HDV) የሚባሉት የቫይረስ አይነቶች ደግሞ በዋናነት የሚተላለፉትበት መንገድ በሽታዉ ባለበት ደም ንክኪ ምክንያት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ስለሆነም ማንኛዉም ሰዉ በቫይረሶቹ ላለመጋለጥ ከላይ የተጠቀሱትን መተላለፊያ መንገዶች በሚገባ አዉቆ እራስን መጠበቅ ተገቢ ነዉ፡፡

ልክ አይደለም!! ከገፅ 11የቀጠለ

ሁሉም ሰው ያለው ከፊል እውቀት ነው፡፡" ሰው በከፊል እውቀቱ እንኳ ተነጋግሮ መግባባት መቻል አለበት፡፡ በሃሳብ የበለጠ እና የሚያሳምን እስከሆነ ድረስ ሴትም ትሁን ወንድ ሀሳቡ ተቀባይነት ማግኘት አለበት፡፡ ሆኖም ሴትን ማዳመጥ ጊዜ ማባከን እንደሆነ የሚቆጥር እንደዚህ አይነት ሰው ሞልቷል፡፡ የሱን የሀሳብ ድፍድፍ ብቻ በግርድፉ ዘርግፎ መሮጥ ይቀለዋል፡፡

በአጭር ልቦለዱ ላይ ያለችው ሴት በላይዋ ላይ የተፈጸመው ግፍ ሳይበቃ፤ እምነቱን አጎደልኩ ብላ ራሷን ወቅሳ ራሷን አጥፍታለች፡፡ ይህ እንግዲህ የገጠሯን ሴት ህይወት እና አስተሳሰብ ያመለክታል፡፡ ይህን ችለው እና ይህን ሆነው ነው ሴቶች የሚኖሩት፡፡

"አንቺ ግን በጣም አክርረሻል፡፡" "ችግሩ ላይ ሳይሆን መፍትሔው ላይ ብትሰሩ የተሻለ ነው፡፡" አለ ወደ እኔ እየተመለከተ፡፡

ስራው አሁንም ለሴቶች ተወረወረ፡፡ ከሁለቱ አንደኛው ጨዋታው ውስጥ በሀሳብ ዘሎ እንደገባው ሁሉ ሀሳቡን ዳር ሳያደርስ በእግሩ እየነጠረ ክፉዉ ወጣ፡፡

እኔ ግን የጀመርኩትን ሀሳብ ለመጨረስ ቀጠልኩ፡፡

"ለችግሩ መፍትሔ ከሁለቱም፤ ከወንድም ከሴትም ነው መሰጠት ያለበት፡፡"አንዱ ሌላው ጫና በማይፈጥር ሁኔታ ነው ተሳስበው ሕይወታቸውን መምራት ያለባቸው" ወንዱም ሴቱም መማር አለበት፡፡ አስተሳሰባቸን ሲሻሻል ድርጊታችንም ይሻሻላል፡፡ ስለዚህ የሚያስፈልገው ለሁሉም ትምህርት ነው፡፡

እዚህ ላይ አንድ ጓደኛዬን የታዘብኳት ትዝ አለኝ፡፡ እንዲሁ ስለሴትና ወንድ ተነሳና እኩል ናቸው አይደሉም የሚል ተወራ፡፡ እንደ እኔ እኩል ናቸው ሳይሆን የተለያዩ ናቸው፡፡

ግን በሰብዓዊነት እኩል ክብር ይገባቸዋል ባይ ነኝ፡፡ በዚህ መሃል "ሴት ለምን ትመታለች; ብትችል ኖሮ ትመታ ነበር፡፡ አቅም ስለሌላት ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ሴቶች ይደገፉ የሚባለው ነገር አይገባኝም፡፡ ምንስ አድልኦ በደል ደርሶባቸዋል;"አለች፡፡

በጣም ተደነቅሁ፡፡ ይህን ከሴት በመስማቴ ውስጤን በትዝብት ሽምቅቅ አደረገው፣ በባህል ተጽዕኖ ምክንያት እንዳታድግ በኢኮኖሚ እንዳትፈረጥም ፣ በፖለቲካ ድርሻ እንዳይኖራት በማድረግ፣ በሚደረጉ ማናቸውም ቤተሰባዊ፣ ማህረሰባዊም ሆነ ሀገራዊ ውሳኔዎች ላይ ምንም ሚና እንዳይኖራት መደረጓ እንደመብት ገፈፋ አለመታየቱ በተለይም በሴት ገረመኝ፡፡

ሽረ ብዙ የማይገባኝ ነገር አለ፡፡ ተማርን የሚለው ማህበረሰብም ቢሆን አዕምሮው ሲከፈት አለመማሩን ያሳብቅበታል፡፡ አንዱ እንዲሁ የወሊድ ፈቃድ ለሴቶች ስድስት ወር ሊሆን ለፓርላማ ለውሳኔ ሊቀርብ ነው ሲባል ጊዜ በቃ ሴቱ ስራ ላለመስራት እየወለደ ቤቱ ቁጭ ሊል ነው አሉ፡፡ በመጀመሪያ ሴት ብቻዋን አትወልድም፡፡

ወንድና ሴት መገናኘት አለባቸው፡፡ ይህን ማስረዳት ለዲግሪ ምሩቅ ሀሁ ማስቆጠር እንደማለት ነው፡፡ መውለድ የሚወሰነው በሴቷ ብቻ አይደለም፡፡ በዚያ ላይ ከመውለድ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮችም መነሳት አለባቸው፡፡ ቤት መቀመጥ እንደ እድል መቆጠር እና እንደ ስራ ፈትነት መታየቱም ያበግናል፡፡

እናቱ ባትወልደው እሱም እዚህ እንደማይገኝ እንደገና ማስተማር ያስብኝ አይመስለኝም፡፡ ልጅን የመንከባከብና የማሳደግ ትልቅ ሀላፊነት እንደ ስራ መፍታት መቆጠሩ በራሱ ያማል፡፡ ራዲካል ፌሚኒስቶች አይ በቃ ሴት የበታች ሆና እንድትታይ ያደረጋት መውለዷ በመሆኑ ዘር የመተካት ጣጣ በቴክኖሎጂ ይታገዝ ያሉት በከእንዲህ አይነቱ ተልካሻ አስተሳሰብ ተማረው ተልካሻ መፍትሔ ማበጀታቸው ይመስለኛል፡፡

በሌላ ጊዜም በቴሌቪዝን አንድ ፕሮግራም ስንከታተል እንዲሁ ባል ሚስቱን ገደለ የሚል ዘገባ እየቀረበ ነበር፡፡ ምን አድርጋው ነው; እያሉ ሰዎች ይጠይቃሉ፡፡ ምንስ ብታደርገው የመግደል መብት አለውን; ሰብዓዊ የሆነውን የሰው ልጅ የመኖርን መብት መግፈፍ እኮ ነው፡፡

ቢነገሩ የማያልቁ በስርዓተ ጾታ ዙሪያ ትክክል ያልሆኑ አስተሳሰቦችና ድርጊቶች በዓለማችን ላይ በተለይም በአንደኛ ዓይነት ሀገሮች ተንሰራፍተው ይገኛሉ፡፡

እኔ እንደሚመስለኝ የሚበጀው ሁሉም ሰው ነው፤ ሴትም ወንድም ኢፍትሃዊ የሆነ ነገር በቤትም በውጪም በማንም ላይ መድረስ የለበትም፡፡ ሰው የሆነ ሁሉ እኩል የሚጋራው የስውነት መብቱ ሁሉ መጠበቅ አለበት፡፡ በመተሳሰብና በፍቅር ቤተሰብ ይገነባል፣ ማህበረሰብ ይታነጻል ሀገር ይቆማል፡፡

ያ ካልሆነ ግን የሴቷ ምሬት፣ ምሬት የወረረው ዜጋ ወደ ማፍራት ተሸጋግሮ ለቤተሰቡ እና ለሀገሩ ግድ የሌለውን ትውልድ ማስታቀፉ አይቀሬ ስለማሆን በሁሉም ዘንድ ይታሰብበት፡፡

ከቦረቦር መንደር... ከገፅ 15 የቀጠለ

ትተን ዘመትን፡፡ መተከል በቆየሁበት ወቅት በተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ተጠቅቶ ነበር፡፡

ከዘመቻዉ መልስ የሁለተኛ ዓመት ትምህርቴን በመቀጠል በአንደኛዉ ሴሚስትር 3.82 እንዲሁም በሁለተኛዉ ሴሜስተር 4.00 በማምጣት በጠቀላላ ዉጤት (CGPA) 3.87 በማምጣት በእጅግ ከፍተኛ ማዕረግ ከትምህርት ክፍሌ አንደኛ ከጠቅላላዉ ተማራቂ ደግሞ ሁለተኛ በመሆን ተመረቅሁ፡፡

ትምህርቴን ከጨረስሁ በኋላ አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ኮሚሽን ዉስጥ በቴክኒክ ረዳትነት ባገኘሁት ዉጤት ምክንያት በቀጥታ ተመደብሁ፡፡ ለሶስት አመት ያህል (1979-1981 ዓ.ም) እንደሰራሁ ነጻ የትምህርት እድል አግኝቶ በ1982 ዓ.ም ወደ ዩክሬን ተጓዝሁ፡፡

ዩክሬን ስድስት አመት በቀየሁበት ወቅት የሁለተኛ ዲግሪየን በከፍተኛ ማዕረግ (CGPA 3.96) ተመርቄ የ "ወጣት ሳይንቲስት" ክብር አግኝቶ በአገሪቱ ጋዜጣ ስሜ ተናኘ፡፡

ከዩክሬን በ 1987 ዓ.ም እንደተመለስሁ ለአንድ አመት ከስድስት ወር በ ጋምቤላ ግብርና ምርምር ማዕከል እንዲሁም ከሮካቲት 1988 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1993 ዓ.ም በአዴት ግብርና ምርምር ማዕከል በተመራማሪነት አገለገልሁ፡፡

ሆኖም አዴት እያለሁ ገና መጦርና መደገፍ እንደጀመርሁ ጥቅምት 21 ቀን 1990 ዓ.ም ዉዷን እናቴን በሞት ተነጠቅሁ፡፡

እጅግ ስሜቴ ተጎዳ፣ አዘንሁ፡፡ ለእናቴ ሃዘን ያደገዉን ጸዎ ገና ሳልላጭ የእናቴ ምትክ ከሆነችዉ ከዉዷ ባለቤቴ ወ/ሮ ፍቅር አለሙ ጋር ተዋወቀን ተጋባን፡፡

ከባለቤቴ ጋር በ1991 ዓ.ም ክተጋባን በኋላ በ1994 ዓ.ም የነጻ ትምህርት እድል አግኝቶ ወደ ታይላንድ አገር በመሄድ የሶስተኛ ዲግሪ ትምህርቴን መከታተል ጀመርሁ፡፡

ለምርምር ስራዬ ወደ አገር ቤት እንደመጣሁ የመጀመሪያ ልጄን ፍሬማሪያም ይሽነዉን በ1995 ዓ.ም ወለድን፡፡ ይህን ዜና ለአማካሪ ፕሮፌሰሬ ስነግረዉ "ጥሩ የዲግሪ ማሚያ" አገኘሁ ያለኝ አይረሳኝም፡፡ አሁን የ11ኛ ክፍል ተማሪ ናት፡፡

እኔ በሌለሁት ወቅት ልጄን ያሳደገቻትን የባቤቴን እህት መልካም ዳርቻን አመስግናለሁ፡፡

ከልጄ መወለድ በኋላ የምርምር ስራየን ለመጨረስ ወደታይላንድ በመመለስ 4.00 ነጥብ በማስመዝገብ ትምህርቴን ጨርሻ በ1996 ዓ.ም ተመለስሁ፡፡
ወደ አዴት እንደተመለስሁም የማዕከሉ ዳይሬክተር በመሆን ከ1996-1997 ዓ.ም ለሁለት አመት ካገለገልሁ በኋላ ወደ አማራ ግብርና ምርምር ኢንስቲቱዩት በመዛወር በከፍተኛ ተመራማሪነት ከዚያም በአፈርና ዉሃ ምርምር ዳይሬክተርነት ከ1998-2000 ዓ.ም ድረስ አገልግያለሁ፡፡

በ2000 ዓ.ም ሁለተኛዋ ልጄ ቢታንያ ይሽነዉ ተወለደች፡፡ አሁን የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ናት፡፡

በ2001 ዓ.ም ወደ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ረዳት ፕሮፌሰር ሆኜ ተቀጠርሁ፡፡ ከሁለት አመት ቆይታ በኋላ የተባባሪ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ በደረጣን እድገት በ2003 ዓ.ም አገኘሁ፡፡

በነዚህ ጊዜያትም የትምህርት ክፍል ኃላፊና የድህረ-ምረቃ ምርምርና ማህረበረሰብ አገልግሎት ተባባሪ ዲን በመሆን አገልግያለሁ፡፡

የምርምርና ማስተማር ስራዬን በመቀጠል 51 የምርምር ስራዎችን (Journal Articles) በማሳተም፤ 54 የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎችንና 3 የ3ኛ ዲግሪ ተማሪዎችን በማማከር አስመርቄያለሁ እንዲሁም 55 የ2ኛ ዲግሪና 9 የ3ኛ ዲግሪ ተማሪዎችን በተለያዩ ዩኒርሲቲዎች ፈትኛለሁ፡፡

ከዚህ በጠጨማሪም ከ10 የሚበልጡ ፕሮጀክቶችንበመቅረጽና በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ከዉጭ አገር በማስመጣት አርሶ አደሩንና አገሬን የሚደገፍ ሥራ ሰርቻለሁ፡፡ ይህን ስራየን የተመለከተዉ የባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ አመራር ቦርድ ከሚያዚያ 07/2012 ዓ.ም ጀምሮ የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግን ሰጥቶኛል፡፡

ይህም መርዓዊ ላይ ያዉም ከአረቋና ጠላ ሻጭ ምሲኪን ድሃ ተወልዶ ሙሉ ፕሮፌሰር የሆነዉ የመጀመሪያዉ ሰዉ ያደርገኛል፡፡

ይህን ማዕረግ ከተቀበልሁ በኋላ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የድህረ-ምረቃ ፕሮግራም ዲን ሆኜ ያገለገልሁ ሲሆን ከጥቅምት 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የምርምርና ህትመት ዳይሬክቶሬት ተቀዳሚ ዳይሬክተር ሆኜ በማገልገል ላይ እገኛለሁ፡፡

ይኸዉ እንግዲህ ከሚጫ ቦረቦር የተነሳዉ ታሪኬ በፕሮፌሰርነት ተጠናቋል፡፡

በህይወት ዘመኔ ሁሉ በገንዘብ፤ በሃሳብና በሞራል የደገፉኝን ሁሉ አመሰግናለሁ፡፡ በተለይም ለዉዷ እናቴ አጥቢያነሽ ገሠሠ፤ ለባለቤቴ ወ/ሮ ፍቅር አለሙ፤ ለወንድሞቸ ወርቁ ገ/ሥላሴና አንሙት አያና እንዲሁም ለሁሉ ነገሬ መነሻና መሰረት ለሆነዉ ለመርዓዊ አንደኛና መለስተና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ልዩ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

ከኔ በኋላ ያለዉ ትዉልድ ሁሉ እኔ ባለፉትበት ዉጣ ውረድ እንዳያልፍ ምኞቴ ነዉ!!

የሳይንስ ጥግ

ይህ አምድ ሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ነክ የሆኑ ዕሁፎች ይቀርብበታል

የዶሮ ሌጦ

በትዕግስት መኮንን ሂደሚኒቲስ ፋክልቲ

ዶሮ ሲነሳ፤ አመት በዓል፣ ወይም "ሽረ ፈረሰኛ"..... የሚለው የማን አሊቦሽ ዲቦ መዚቃ፤ አለፍ ካለም ተደልሎ የሚያውቅ ሰው "ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት" የሚለው አባባል ትውስ ይልም ይሆናል:: አልያም እንቁላሏ... ሌላም ሌላ... ከዶሮ ጋር የተያያዘ ነገር ሊመጣልን ይችላል፡፡

'ከዶሮ ቆዳ የተለያዩ የቆዳ ውጤቶች መስራት የቻለ ጀግና' የሚል ዜና ብታነቡ ግን እንደኔ መደመማችሁ አይቀሬ ነው ብየ እገምታለሁ፡፡

እንዴት ሊሆን እንደቻለ ለመጠየቅ ጉጉት አድሮብኝ ወደ ጉዳዩ ባለቤት አቀናው ላካፍላችሁም ወሰንኩ::

የጉዳዩን ባለቤት ከማስተዋወቁ በፊት ስለ በኢትዮጵያ ቴክስታይል ፋሽን ዲዛይን ኢኒስቲዩት የሌዘር ኢንጂነሪንግ ትምህርት ክፍል እና ስለ ቆዳ ኢንዱስትሪ ጥቂት ነጥቦች ላንሳላችሁ::

የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ በሙሉ ቆዳና በከፊል-የቆዳ ምርት ዘርፍ በተለያዩ ቅርጾች ማቀነባበሪያ ቆዳዎች ፣ የጫማ ቆዳዎች ፣ የቆዳ አልባሳት ፣ የጀርባ ቦርሳዎች፣ የኪስ ቦርሳዎች ፣ የኢንዱስትሪ ጓንቶች እና የተጠናቀቀ ቆዳ ጨምሮ የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ላይ ይገኛል፡፡

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ የጨርቃጨርቅና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በቆዳ ኢንጂነሪንግ ፕሮግራም የሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪ መጀመሩ ይታወሳል፡፡ በአሁኑ ወቅት በቆዳ ልማት ኢንጂነሪንግ ፣ በቆዳ ምርት ኢንጂነሪንግ እና በቆዳ ልማት ምርት የሁለተኛ ዲግሪ በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በግብርና መር እና በኤክስፖርት ላይ የተመሠረተ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂውን እንዲሁም የጨርቃ ጨርቅ፣ የቆዳ እና አልባሳት ማምረቻ ችግርን መፍታት፣የኢትዮጵያ ባህላዊ የቆዳ ዲዛይንን በማሻሻል አዳዲስ ስርዓቶችን እና ዕድሎችን በመፍጠር ተግባራዊ የማድረግ ዓላማ አንግቦ እየሰራ ይገኛል::

ከዶሮ ቆዳ የተለያዩ የቆዳ ውጤቶችን የሰራው ጀግና ዘሪሁን ተሾመ ይባላል ከዚሁ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ዲግሪውን ተምሮ በትሪት ክፍሉ በመምህርነት እና ምርምር እያገለገለ ይገኛል፡፡

ከመሥያው ራቅ ያልኩ ስለሆንኩ እና የዶሮ ቆዳ ጫማ እና ቦርሳ ይሰራብታል ብሎ ለመቀበል የተቸገርኩ መሆኔ እንዳይታወቅብኝ ፈራ ተባ በማለት፤ "ግን እንዴት አሰብከው? በማለት ጥያቄየን ጀመርኩ፡፡

የመጀመሪያ ዲግሪየን በሌዘር ኢን ጅነሪንግ ነው የተመረኩት እናም በሌዘር ዙሪያ የተፃፉ ዕሁፎችን እና ትንቢት ነክ(prediction) የሆኑ መፅሀፎችን ማንበብ ስለምወድ በቂስ በሊና ሳርካ የተፃፈውን "የኢትዮጵያ ከፍታ" የሚል መፅሀፍ በማነብበት ወቅት ስለዶሮ ቆዳ የሚናገር አንድ መስመር አነበብኩ በዛች መልዕክት ምክንያት ስለ ዶሮ ቆዳ የበለጠ የማወቅ ጉጉት አደረብኝ፡፡

ከዛምበዶሮቆዳዙሪያየተፃፉዕሁፎችን እና ጥናቶችን ማንበብ ቀጠልኩ ይላል ዘሪሁን አነሳሱን ሲያጨውተኝ፡፡

ከዛስ በሚል መልእክት አይኖቼን አፍጥጨማዳመጤንቀጠልኩቀጣዩን ሂደት ለማወቅ በሚያሳብቅ መልኩ፤ ቀጥዬ አለ ዘሪሁን ቀጥዬ preliminary test(የመጀመሪያ መከራ) ለመስራት ወሰንኩ እና ቤት ውስጥ ለበዓል የተገዙ ዶሮዎችን ተጠቅሜ መክራ ጀመርኩ፡፡ የሌዘር ኢንዱስትሪ ላብራቶሪን ተጠቅሜ አባይማዶ ከማገኘኝ አብርሀም ከሚባል ዶሮ አርቢ ግብአቶችን በመውሰድ ጥናት አካሄድኩና መስራት እንደሚቻል አረጋገጥኩ፡፡

የዶሮ ቆዳ በተለምዶ እንደምናየው በጣም ስስ እና ጭንቅ የማይችል ይመስላል፤ እንዴት ጫማ እና የተለያዩ የቆዳ ውጤቶችን መስራት ይችላል በሚል ጥያቄየን አስከተልኩ፡፡

መልሱ መቻልስ ይቻላል ይልቁስ እንዴት የሚለውን ለመረዳት በጥሞና አዳምጥ ዘንድ፣ በሚጋብዝ መልኩ፤ "ሲሚንቶ ዱቄት እና ብናኝ ቅንጣት ነው አይደል?" አራሴን ወደ ላይ እና ወደ ታች ነቀነኩ፣ "ነገርግን የሚገራርሙ ህንፃዎችን የማቆም ሀይል አለው" በማለት ጀመረና ስለሳይንሱ ማብራራት ቀጠለ፡፡

በመሰረታዊነት ቆዳን ቆዳ እና ሌጦ በማለት በሁለት አይነት እንከፍለዋለን::የተላልቅ እንሰሳት ማለትም ከብት፣ ግመል፣ ጎሽ የመሳሰሉት ቆዳ ሲባሉ የትናንሾች እንሰሳት እንደ አዞ፣አሳ፣ሰጎን እና መሰል እንሰሳት ቆዳ ደግሞ ሌጦ እንለዋለን፡፡

የሌጦ ውጤቶች በተለይም የአሳ፣አዞ እና የሌሎች ተሳቢ እንሰሳት በአደጉ አገሮች በጣም ውድ ዋጋ ለሚያወጡ የቅንጦት እቃዎች መስሪያ ይገለገሉባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ከጎረቤት አገር ኬኒያ የአሳ ሌጦ ይጠቀማሉ፡፡

አገራችን የአዞ ሌጦ የውጭ ምንዛሬ ያመጣል ያለው ዘሪሁን ወደ ውጤት ቀይሮ ቢላክ ምን ያህል ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ማምጣት ይቻል እንደነበር በቁጭት ጠቀሟል፡፡

ወደ ዶሮ ቆዳ ጥናቱ ዝርዝር ሂደት ማብራሪያ ሲመለስ በመጀመሪያ ቆዳው ውስጥ ምን ምን ንጥረ ነገሮች ይገኙሉ የሚለውን አጠናሁ፤ ቀጥዬ ኬሚካሎችን መቋቋም ይችላል የሚለውን አየሁ በአጠቃላይ ቆዳ ከ20 እስከ 30 የሚሆኑ የተለያዩ ደረጃዎችን(-steps) አልፎ ነው ውጤቱን የምናየው በማለት አስረዳኝ::

ዶሮ ቆዳ በተለይም እግሩ የራሱ የሆነ ቅርፅ(Texture) እና ውበት ስላለው ከሌሎች እንሰሳት የተለየ ያደርገዋል፡፡

"እግሩንም ነው እንዴ የምትጠቀመው?" አልኩ በግርምት፤ "ያው... የዶሮ እግር ከአስራ ሁለት ብልቶች ስለማይቆጠር ጥቅም አለው ብሎ ለማሰብ ተቸግሬ ነው!" ሳቅ
አወ እግሩማ ዋናው ነው በቆዳው ላይ በተፈጥሮ ያለው ቅርፅ በፋብሪካ ሂደት ተጨማሪ ቅርፅ ለማምጣት የሚሰራውን ስራ ስለሚያስቀር እና በራሱውብስለሆነየበለጠይጠቅማል፡፡

ሌላው የዶሮ ቆዳ ሙቀት በመከላከል ረገድ ከሌሎች 70% የተሻለ አቅም አለው ይላል፡፡ የስራቸውን የዶሮ ቆዳ ውጤቶች ኤግዚብሽን ላይ ማቅረቡን እና ለተለያዩ ድርጅቶች በማሳየነት እንደሰጠ ነግሮኛል፡፡ ከሳይንሳዊ ትንታኔው ባሻገር የጥናቱን ውጤት ወደ ምርት እና ቢዝነስ ለመቀየር የሄደበትን

እርቀትም አጫውቶኛል፡፡

ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር አጋር በመፍጠር ወደ ምርት ለመግባት ኤልፎራ እና ደብረዘይት የሚገኙ የዶሮ ቆዳ ውጤቶች እና በቀን ከአራት እስከ አምስት ሽህ ደሮዎችን የሚያርዱ የዶሮ አርባታ ድርጅቶችን በግብዓትነት ለመጠቀም ማቀዱን ይናገራል፡፡

ትኩረታችን በአለም ገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን ልዩ(unique) በመሆን የራሳችንbrand(መለያ)በመፍጠር በውጭ ገበያ መቅረብና ተወዳጅነትን ማትረፍ ነው ይላል ዘሪሁን:: በስራው ላይ ስላጋጠመው

ዘሪሁን ተሾመ
ሌዘር ኢንጂነሪንግ መምህርና ተመራማሪ

ተግዳሮትም ጠይቄዋለሁ፤ አዲስ ነገር ስታስቢ ሁለት ነገሮች ይገጥሙሻል፤ በማለት ጀመረ፤ "ስማየት መንጎት እና ግራ መጋባት" በአደጉት አገራት አዲስ ነገር ይዘሽ ስትመጭ ፈጠን ብለው ምላሽ መስጠት እና በመደገፍ ውጤት እንዲያመጣ ያደርጉታል:: እኛ ሀገር ግን በብዛት ግራ ከመጋባት ባሻገር ቢሮክራሲው ፈተና ሆኖብኛል ይላል፡፡ የቦታ እና የገንዘብ እጥረትም ተጨማሪ ተግዳሮቶች እንደሆኑበትገልጾልኛል::

የዘሪሁን የምርምር ውጤት እና ራዕይ ከተለመደው ነገር ወጣ ብለን በማሰብ እና በመመራመር ራሳችንን ብሎም ሀገራችን በአለማቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ማድረግ እንደሚቻል ያሳያል፡፡

ዘሪሁን ከዶሮ ቆዳ ያመረታቸው ፣ጫማ እና የቁልፍ መያዣዎች

ስብጥር

ይህ አምድ በሌሎች አምዶች ያልተስተናገዱ ልዩ ልዩ ዕሁፎች ይቀርብበታል

የቆጋ መስኖ የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ብዜት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ማዕከል ከየት ወደ የት

በወንዳለ ድረስ

በምዕራብ ጎጃም ዞን ሰሜን ሜጫ ወረዳ የሚገኘው የቆጋ መስኖ ፕሮጀክት አማራ ክልል ከሚገኙ ሰፊ የልማት ጣቢያዎች በዋነኝነት ይጠቀሳል፡፡ በርካታ ቁጥር ያላቸውን የአካባቢው አርሶ አደሮችም ተጠቃሚ አድርጓል እያደረገም ይገኛል::

ከጠቅላላ ፕሮጀክቱ የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ በግብርናው መስክ የበኩሉን አስተዋፆ ለማድረግ 54 ሄክታር መሬት ከአብክመ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ ለ30 ዓመት በሚቆይ ኪራይ ውል መረከቡ ይታወሳል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ማዕከሉን ከተረከበ ወዲህ በተለያዩ የሰብል ዓይነቶች ከተሸፈነ ሰብል ምርት በተጨማሪ በሰርቶ ማሳያዎች ማለትም በእንስሳት መኖ ልማት፣ በውሃ አጠቃቀም፤እንዲሁም በጥናትና ምርምር በድህረ-ምረቃ ተማሪዎችና በመምህራን የስብጥር ሰብል ልማት፣ የአፈርና ውሃ እና ሌሎች የምርምር ሙከራዎች ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን የመስክ ምልከታ በባለሙያዎች ተካሂዷል፡፡ ምልከታውን ዚጋቢው በስፍራው ተገኝቶ ተመልክቷል፡፡
በዕዕዋት ሳይንስ ትምህርት ክፍል

የማዕከሉ አስተባባሪ አቶ ሃይሌ አለባቸው

መምህርእና የግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ የድህረ ምረቃ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ዲን ዶ/ር ተስፋየ መላክ እንደገለፁት በታው በአራት አቅጣጫዎች ማለትም አማራት፣ አንድነት፣ አንዐ መስክ እና ኩድሚ የሚገኝ ሲሆን አማራት ተክለ ድብ ላይ በአስራኤል ሀገር ውጤታማነታቸው የተመሰከረላቸው ሀስ እና ኢቲንገር ዝርያዎች 4 ሺ 989 የአቦካዶ ችግኞች በክልል ደረጃ የአረንጓዴ ልማት በተጀመረበት ዕለት ግንቦት 30/2012 ዓ.ም ተተክለው ከ97% በላይ የሚሆኑት መዕደቃቸውን የግብርና ባለሙያወች በመስክ ምልከታው ነግረውናል፡፡

አቦካዶው ከአንድ ዛፍ ላይ የሚያገኘው አቲንገር ለአካባቢው ፍጆታ በማዋል የመቀንጨር አደጋን ለመከላከል የራሱን አስተዋፆ ያደርጋል፡፡

የሀስ ምርት ለውጭ ገበያ ለማዋል ታሳቢ ተደርጎ ለተጠቃሚዎች ያመች ዘንድ ከችግኝ ተክላ ጀምሮ ፍሬ እስከሚጥሸጥ ያለው ሂደት በሶፍት ኮፒ አየተዘጋጀ ነው:: አተክከሉ 4በ6 ሜትር ሲሆን ይህም የሆነው አንድ ዝርያ ሲያረጅ በምትኩ ለመትከል እንዲያመች ነው፡፡ሌላው አትክልቱ ውጤት ላይ ሲደርስ ምርት ማመላለሻ 8 ሜትር መንገድ ያለው ሲሆን በሌሎች አገሮች ባልተለመደ ሁኔታ አመቱን ሁሉ መለቀም የሚችል ነው፡፡በዋናነትየሀስ እና ኢቲንገር ዝርያዎች በንጥረ ነገር እና በዘይት ይዘታቸው ከፍተኛ ከመሆናቸው ባሻገር በዓለም አቀፍ ገበያ ተመራጭ ናቸው፡፡

የግብርና ሳይንስ ኮሌጅ መምህራን በመስክ ምልከታ ወቅት

በችግኞች ዙሪያ ፍሩቱን ላቫን የተባሉ ዝርያዎችን ለምርምር ስራ እና ለወንዴ የዘር ምንጭ የሚውሉ ችግኞች መተከላቸውን ጠቁመዋል::

አንድነት ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የተመለከትነው የነጮ እና ሜጫ የዳጉሳ ዝርያን በመስመር እና በብተና በሁለት ሄክታር በመዝራት ልዩነቱን ለአርሶ አደሩ ማሳየት እና የተሻለውን ለአርሶ አደሩ የማስፋት ስራ መሰራቱን ለማየት ችለናል፡፡

አንድነት እና አንዐ መስክ ሰፋፊ ቦታዎች ስለሆኑ ሽዶችን በመስራት እና የጠብታ መስኖ በመጠቀም የተለያዩ የዘር አይነቶችን በማባዛት የአካባቢውን የዘር ፍላጎት በማሟላት የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ ታቅዷል፡፡

የጠብታ መስኖ 50% ውሃ የሚቆጥብ ሲሆን ከአርሶ አደሩ የምንሻማውን ውሃ በመቆጠብ አርሶ አደሩ እንዲማርበት ይደረጋል ብለዋል:: ሌላው የማዕከሉ ክፍል ኩድሚ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኝ ሲሆን በዋናነት ለምርምር እና ማስተማሪያ መሆኑን ገልፀውልናል::

በግብርና እና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ የዕዕዋት ሳይንስ ቴክኒካል አሲስታንስ እና የቆጋ የመስኖ የምርምርና ቴክኖሎጂ ብዜት ማዕከልአ ስተባባሪ አቶ ሃይሌ አለባቸው እንዳሉት የማዕከሉ ዓላማ በቆጋ እና መሰል ስነ ምህዳር ባላቸው አካባቢዎች

ተስማሚነት ያላቸውን የምርምር ስራዎችን ሰርቶ፣ውጤቱን ምቦማላመድ ለማሰራጨት ነው፡፡ በዚህም የምርምር ስራ፣ ቴክኖሎጂ ብዜትና ተማሪዎች ከንድፈሃሳብ ባሻገር የተግባር ትምህርት እንዲሰሩበት ያግዛል፡፡

ዩኒቨርስቲው ከኩድሚ ሳይት 8 ሄክታር ውጪ ባለው መሬት ከ700 መቶ ኩንታል በላይ በቆሎ እና ጤፍ ምርት በማምረት በወቅቱ በአገራዊ ጉዳይ ለተፈናቀሉ ዜጎች ለዕርዳታ ማዋሉን አውስተዋል፡፡በተጨማሪም በኩድሚ አካባቢ

በአፈር ለምነት፣ ሰብል ልማት፣ በእትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም በእንስሳት መኖ ማሻሻያ ስራዎች ዙሪያ ከ23 በላይ የምርምር ስራዎች እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከያዝነው ዕቅድ አንፃር ከተቀመጠው ግብ ደርሰናል ማለት ግን አይቻልም ብለዋል፡፡

ሌላው የቴክኖሎጅ ሽግግርን ታሳቢ ያደረገ የረጅም ጊዜ እቅድ በመያዝ በፀሀይ ሀይል (ሶላር) የሚሰራ የጠብታ መስኖ በመጠቀም ውሃን መቆጠብና ውሃው በሚፈስግበት ቦታ ላይ ማዳረስ እና ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያ መጠቀም እንዲሁም

የአቦካዶ ዝርያዎች በከፊል

ከእንሰሳት ጋር በማስተሳሰር የንብ ቀፎዎችን የማስቀመጥ ስራ ለመስራት ታስቧል፡፡

በአጭር ግዜ እቅድ ደግሞ ኩድሚ አካባቢ ያለው 8 ሄክታር ለምርምር ሲውል አንዐ መስክ እና አንድነት መስክ ስፋት ያለው መሬት የዘር ብዜት ስራ ይሰራበታል፡፡ በዚህ አመት አገልቶ የሚባል የስንዴ ዝርያ በ11 ሄክታር ለማባዛት መስራት ዘር ተገኝቷል ከዚያ ውጪ ቢኤች 540 እና ቢእች 546 የተባሉ የበቆሎ ዝርያዎች በዚህ አመት ለመዝራት አቅደናል፡፡

በሙከራ ደረጃ የዘራነው የዳጉሳ የዘር ብዜት የአማራ ክልል የዘር ብዜት ተቋም ማለፉን አረጋግጦልናል፤ ክልሉ ላይም ምርጥ ዘር ባለመኖሩ በሰፊው የምንሄድበት ይሆናል፡፡ስለ ማዕከሉን ተጨማሪ መረጃ በመያዘ በሌላ ዕትም እንመለሳለን፡፡ ቸር ይግጠመን!

እንግዳ

ይህ አምድ የዩኒቨርስቲው ሰራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ታዋቂ እና ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች በዕንግድነት ይቀርቡበታል

ይሽነዉ ገ/ሥላሴ መንገሻ (ፕሮፌሰር)

ከቦረቦር መንደር እስከ ፕሮፌሰር

የተወለድኩት በሜጫ ወረዳ መርዓዊ ከተማ 01 ቀበሌ ነዉ፡፡ እድገቴ እንደ አብዛኛዉ የመርዓዊ ልጅ በድህነት የተተበተብ ነበር፡፡ እናቴ ወ/ሮ አጥቢያነሽ ገሠሠ ስትባል አባቴ ደግሞ ወ/ር ገ/ሥላሴ መንገሻ ይባላል፡፡
አባቴ ከሸዋ መርሐቤቴ መጥቶ በመርዓዊ ከተማ ፖሊስ በመሆን አገልግሏል፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ አባቴ ወደ ጅጋ ከተማ በመዛወሩ ምክንያት ለተወሰኑ አመታት ከእናቴ ጋር በዛዉ ቆይቻለሁ፡፡

ነገር ግንእናቴና እኔ ንዳድ (ወባ) በተባለ በሽታ በተደጋጋሚ በመታመማችን ምክንያት ወደ መርዓዊ ይዛኝ ተመለሰች፡፡ ይህም የሆነዉ ገና የሶስት ዓመት ልጅ እያለሁ ነዉ፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የእናት እንጀ የአባት ፍቅር አላገኘሁም፡፡

ወደ መርዓዊ ከተመለስን በኋላ እናቴ እንደ አብዛኛዉ የመርዓዊ ምስኪን ሴቶች አረቄና ጠላ በመሸጥ እኔን ወንድሜንና እርሷን ለማስተዳደር ብዙ ደክማለች፡፡

ምንም እንኳ በምግብ እጥረት ምክንያት የመቀንጨር ችግር ስለነበረብኝ የሰፈሩ ባለጠጋ ልጆች "ሲባ" እያሉ ይጠሩኝ የነበረ ቢሆንም ከጓደኞቸ ጋር አጓት ዉሃ በመሄድ እንጭት በመልቀም እናቴን ለማገዝ ሞክሪያለሁ፡፡

አንዳንድ ጊዜ አጓት ዉሃ ጫካ ዉስጥ እያለን ዝናብ ከዘነበ በጎርፍ የተሸረሸረዉን ቦረቦር እንጨት ተሸክሜ ለመሻገር ስለማልችል አብሮ አደጌ እንዳልካቸዉ ናዑድ ያሻግርልኝ ነበር፡፡

ትምህርት አጀማመሬ ከህዝባዊ ኑሮ እድገት ዘመቻ ጋር የሚያያዝ ሲሆን በዚያን ወቅት አሁን የወረዳዉ አስተዳደር ጽ/ቤት ካሰበት አካባቢ ፊደል መቁጠር ጀመርሁ፡፡

ከትምህርት መልስ ግን ከአብሮ አደጌ አበበ ታፈረ ጋር መኪና መንገድ ላይ ጠጠር በመልቀምና ወደበረድ ወንዝ በመሄድ እራሳችንን ለአደጋ የሚያጋልጥ ተግባር መፈጸማችንን የተገነዘቡት ፍታዉራሪ ታፈረ ይማም ወደመርዓዊ አንደኛና መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ትመህርት ቤት ሊያስገቡን ወሰኑ፡፡ በዚያን ወቅት እድሜያችን ከአምስት አመት ስለማይበልጥ የግራ ጆሯችንን በቀኝ እጃችን ከራሳችን በላይ አዙረን ለመንካት ባለመቻላችን በወቅቱ የነበሩት ርዕሰ መምህር ስድስት አመት አይሞላቸዉም ብለዉ አይገቡም ብለዉን ነበር፡፡

ሆኖም ፍታዉራሪ ታፈረ የልጆቼን እድሜ የማዉቀዉ እኔ ነኝ እጃቸዉ አጭር ሆኖ ነዉ እንጅ ስድስት አመት አልፏቸዋል ብለዉ በ1965 ዓ.ም ትምርት ቤት አስገቡን፡፡

በትምህርት ቤት ዉስጥ ደብተር ከማይጥሉ፤ ከማይረብሹ፤ ትምህርት ባግባቡ ከሚከታተሉ ልጆች አንዱ ነበርሁ፡፡ የሰነፍ ተማሪዎች መቅጫ የአድዩ ጨንገር ቆርጬ እንዳመጣ ብዙ ጊዜ መምህራን ይልኩኝ ነበር፡፡

በትምህርቴም ጥሩ በመስራቴ ከ4ኛ ወደ 6ኛ ዳብል አልፌ ነበር፡፡

በሩጫ ፈጣን ከመሆኔ የተነሳ የእግር ኳስ ክህሎቴ የላቀ ስለነበር በ "ሌባና ፖሊስ" ጨዋታም ሆነ በኳስ ጨዋታ እኔ ያለሁበት ቡድን ብዙ ጊዜ አይሸነፍም ነበር፡፡ "ሌባና ፖሊስ" ስንጫወት አበበ ታፈረና ይሽነዉ እዉነቱ ግንባር ለግንባር ተጋጭተዉ የተጎዱት ጉዳት የአበበን የተፈነከተ ግንባር አሁንም ባየሁት ቁጥር ትዝ ይለኛል፡፡

ቦረቦር ሜዳ ኳስ መጫዎቻችን ነበር፤ ብዙም ሩጠንበታል፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ኳስ ስንጫዎት ኳሷ ወደእማ ጠጀ አጥር ግቢ ዉስጥ ገባች፡፡ በወቅቱ አጥር ከነበራቸዉ ባለጠጎች አንዷ እማ ጠጀ ነበረች፡፡
ኳስ በመፈለግ ላይ እያለን አንድ እንደ ጣሳ የመሰለ ነገር አገኘን፡፡

ምንነቱን ለማወቅና በዉስጡ የተደበቀዉን ሿሿ የሚል ነገር ለማዉጣት መክራ ላይ እንዳለን እኔና አንዳንድ ጓደኞቼ ወደየቤታችን ተጠራን፡፡ ቤት ስደርስ የፍንዳታ ድምጽ በመስማቴ ወደፎረፎር ሜዳ ስመለስ ሜዳዉ ደም በደም ሆናል፡፡ ያገኘነዉ ጣሳ መሰል ነገር ለካ ቦንብ ኖሯል፡፡

በዚህ አደጋ ቦጋለ መላክ የተባለ ብላቴና ሁለት እግሩንና ሁለት እጁን ሲያጣ፤ ሃይማኖት አስረስና አበበ አንዱዓለም መጠነኛ ጉዳት የደረሰባቸዉ ነበሩ፡፡

በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ የሚገኘዉ ዶ/ር አበበን አንዱዓለም በትምህርቱ እጅግ ጎበዝ ስለነበር እንዲያ ያደረገዉ በሰዉነቱ የገባዉ ባሩድ ይሆናል እያልን እናማዉ ነበር፡፡ ቦጋለ ግን አካሉን አጥቶ አዲስ አበባ ለገሃር አካባቢ ሲለምን በአንድ ወቅት አግኝቸዉ ነበር፡፡
የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን በ1971 ዓ.ም ከጨረስኩ በኋላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ለመቀጠል ወንድሜ አቶ ወርቁ ገ/ሥላሴ በመምህርነት ሲሰራበት ወደነበረዉ ፍኖተሰላም በ1972 ዓ.ም ተጓዝሁ፡፡

ነሮየ የተስተካከለ አልነበረም ፡ የራብና ጥማት ቅጣት ተፈጽመብኝል ፡ ለጥናት የማበራዉ ኩራዝ ኮርኔስ ያጠቀራል ተብሎ ተጥሎብኝል

ፍኖተሰላም በነበርሁበት ወቅት ዘጠነኛ ክፍል 4ኛ ደረጃ ያገኘሁበት የተሻለዉ ዉጠቴ ሲሆን ከ10ኛ-12ኛ ባሉት ክፍሎች ከ10ኛ በታች ያሉትን ደረጃዎች አግኝቻለሁ፡፡

ኑሮየ የተስተካከለ አልነበረም፡ የራብና ጥማት ቅጣት ተፈጽሞብኝል፡፡ ለጥናት የማበራዉ ኩራዝ ኮርኔስ ያጠቀራል ተብሎ ተጥሎብኝል፡፡

ከቤተሰቡ አባላት በተለየ ሁኔታ ልብሴን የማጥበዉና ገላየን የምታጠበዉ አራራ ወንዝ በመሄድ ነበር፡፡ የአራራ ወንዝ ዉስታ አይረሳኝም፡፡

ከዚህ የመከራ ኑሮየ በኋላ በ1975 ዓ.ም ማትሪክ ተፈተንሁ፡፡ ነገር ግን ዉጤቴ ሲመጣ 2.0 ነጥብ መሆኑን ተረዳሁ፡፡ በዚህ ወቅት በጣም አዘንሁ፤ ተበሳጨሁ ነገር ግን ተስፋ አልቆረጥሁም፡፡ ሳይደግስ አይጣላ እንዲሉ አሥር ዓመት አስመራ የኖረዉ ወንድሜና ባለዉለታየ አሥር አሰቃ አንሙት አያና በ1975 ዓ.ም መጨረሻ ተዛዉሮ ወደፍኖተ ሰላም መጣ፡፡

ወንድሜ እኔን ሲያገኘኝ ደነገጠ፡፡ ስራ አጥ፤ ሲያገኝ የሚበላ ሲያጣ ጾሙን የሚያድር ቀጫጫ የጎዳና ልጅ ሆኖ አገኘኝ፡፡ ወንድሜም ቤት ተከራየና አብረን መኖር ጀመርን፤ እንደሰዉም ምግብ ለመመገብ በቃሁ፡፡

ከወንድሜ ጋር ከተመካከርን በኋላ እንደገና አጥንቶ ዩኒቨርሲቲ መግባት እናዳለብኝ ወሰንሁ፡፡ ነብዩ እንዳሳማዉ ከሚባልና አብሮኝ የማትሪክ ቁስለኛ ከሆነዉ ጓደኛየ ጋር አብረን በማጥናት በ1976 ዓ.ም ማትሪክ ተፈተን፡፡ ሆኖም ፈተና ጨርሰን ከግቢ ስንወጣ ለብሄራዊ ዉትድርና ታፍሰን የጭነት መኪና ላይ ተጫንና ቀበሌ ዉስጥ ካለ መጋዝን ዉስጥ ከተቱን:: በሚቀጥለዉ ቀን የቁመና ግምገማ ሲደረግ እኔ ቀጭንና በክብደቴም ቀላል ስለነበርሁ ስወድቅ ጓደኛየ አለፈና ወታደር ሆነ፡፡

የማትሪክ ዉጤት እስኪመጣና ለብሄራዊ ዉትድርና ዘመቻ ድጋሚ እንዳልታፈስ ጅጋ አባቴ ቤት ተደበቅሁ፡፡

ከዚያም የማትሪክ ዉጤት መጣና 2.8 ነጥብ አመጣሁ፡፡ ይህ ነጥብ ለመደበኛ ተማሪዎች የዲግሪ መግቢያ የነበረ ቢሆንም በግል ለተፈተንሁት እኔ ግን የዲፕሎማ መግቢያ ነበር፡፡

የግል አመልካቾችን ፎርም ሞልቶ ስጠባበቅ በአዲስ አበባ ዩኒርሲቲ ስር ይተዳደር ወደነበረዉ አዋሳ ግብርና ኮሌጅ መመደቤን ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ አነበብሁ፡፡ አዋሳ ለመሄድ ዝግጅት አደረግሁ፡፡

ወንድሜ አንሙት በህይወቱ የመጀመሪያዉ የሆነዉን ችፖሊኒ ቆዳ ጫማ፤ ቦላሌ፤ ሽሚዝና ሹራብ ገዝቶ መሳፈሪያ ብር ሰጥቶ ወደ አዋሳ ሸኘኝ፡፡ ወደ አዋሳ በመሄድ ላይ እያለሁ አዲስ አበባ አድራ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜም ሎተሪ አሟሪ መስለዉ መሰረት ትምህርት አስተምራ ባጠራቀምሁት ገንዘብ የገዛሁትን ኦርየንት ሰዓት የወሰዱብኝ አይረሳኝም፡፡

አዋሳ ግብርና ኮሌጅ ስገባ ሰዉ መሆን እንዳለብኝ ለራሴ ቃል ገባሁ፤ ትልቅ ደረጃ ለመድረስ ከራሴ ጋር ተስማማሁ፡፡
በ1977 ዓ.ም የአዋሳ ትምህርቴን በትጋት መማር ጀመርሁ፡፡

በአንደኛዉ ሰሜስተር 3.69 በሁለተኛዉ ደግሞ 3.90 አመጣሁ፡፡ ከዚያም ወደ መተክል የሰፈራ ቤት ስራ ዘመቻ ተጠርተን ትምህርታችንን

ወደ ገፅ 12 ዞሯል

Rediet Mesfin
PhD in SPECIAL NEEDS EDUCATION

Medhanit Belachew
PhD in TEFL

Selamawit G/Egzabher
PhD in Economics

Fitsum Dechasa
PhD in Development Studies

Fikrte Demissie
PhD in environmental planning

Mulugojam Wondyfraw
PhD in Urban dev't Environmental and Socio-economic issues.

zewdie Tamrie
PhD in TEFL

Selomie Zewdalem PhD
in TeAm

Aynalem Girma
PhD in Linguistics